ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ሐሙስ
82ኛ ዓመት ቁጥር 215 ሚያዝያ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በዓመት ሦስት ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ
## የሚያመርት ፋብሪካ ሊገነባ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**


ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- በዓመት ሦስት ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ የሚያመርት የሲሚንቶ፣ የብረትና የኖራ ፋብሪካ በድሬዳዋ መልካ ጀብዱ በቅርቡ ሊገነባ መሆኑን የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ እየታዩ ያሉ የግንባታ ግብዓት ችግሮችን በማምረት እና የግብይት ሥርዓቱን በማዘመን እንደሚፈታም ተጠቁሟል፡፡

የናሽናል ዌስት ኢንተርናሽናል ሆልዲንግ በድሬዳዋ በሚያስገነባው የመልካ ጀብዱ የሲሚንቶ፣ ብረት እና ኖራ ፋብሪካ ግንባታ ስምምነት ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ እንደገለጹት፤ የሚገነባው ፋብሪካ ከሀገሪቱ የግንባታ ግብዓት ፍላጎት እስከ 19 በመቶ የመሸፈን አቅም ያለው ነው፡፡

የኮቪድን ወረርሽኝ ጨምሮ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው እጥረቶች እንደተጠበቁ ሆነው በግንባታ ግብዓቶች እጥረት ማምረት ባለመቻላችን የተሸከምናቸው ብዙ ፈተናዎች አሉ ያሉት ሚኒስትሯ፤ ዘርፉን ከዋጋ ንረት ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች ፈታኝ አድርገውታል ሲሉም አክለው ገልጸዋል፡፡

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የግንባታ ግብዓቶችን ማጠናከርና በማበረታታት የማይተካ ሚና እንደሚጫወቱ በመጥቀስ፤ “እየታዩ ያሉ የግንባታ ግብዓት ችግሮችን በማምረት እና የግብይት ሥርዓቱን በማዘመን እንፈታለን ” ብለዋል፡፡

በዓመት ሦስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ
በመጪዎቹ ሁለት ዓመታት ከስድስት በመቶ በላይ ዕድገት ያስመዘግባል

ገጽ 3



## በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት ዘርፎች አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ከፖለቲካ ዲፕሎማሲ በተጨማሪ በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲውና በውጭ ግንኙነት ዘርፎች አበረታች ውጤቶች እየተገኙ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲና ... ወደ ገጽ 16 ዞሯል

# በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር 6 ነጥብ 3 ቢሊዮን ችግኞች ሊተከሉ ነው

- እስካሁን 5 ነጥብ 4 ቢሊዮን ችግኝ ተዘጋጅቷል

**መስከረም ሰይፉ እና አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ስድስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ችግኞች በተለያዩ አካባቢዎች እንደሚተከሉ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ፕሮፌሰር ኢያሱ ኤልያስ ትናትና በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር

በአረንጓዴ አሻራ ... ወደ ገጽ 16 ዞሯል

# “ባለውለታ የሆኑ የልዩ ኃይል አባላት እንዲበተኑ ሳይሆን ወደላቀ ተልዕኮ እንዲሸጋገሩ ነው የተፈለገው"

-ሰማ ጥሩነህ (ዶክተር)
በአማራ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የአስተዳደር ጉዳዮች ክላስተር አስተባባሪ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ባሕር ዳር፡- የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀቱ ውሳኔ ባለውለታ የሆኑ የልዩ ኃይል አባላት እንዲበተኑ ሳይሆን ወደላቀ ተልዕኮ እንዲሸጋገሩ ተፈልጎ መሆኑን በአማራ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የአስተዳደር ጉዳዮች ክላስተር አስተባባሪ ሰማ ጥሩነህ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ባለውለታ የሆኑ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዜና



ፎቶ - ዳኜ አበራ

አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶክተር)

# በአደጋ ስጋት አመራር ሥራዎች ላይ የኮሙኒኬሽን ሙያተኛው ባለቤት ሆኖ ሲሠራ ይገባል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዳማ፡- እንደሀገር በሚያጋጥሙ የአደጋ ስጋት አመራር ሥራዎች ላይ እያንዳንዱ የኮሙኒኬሽን ሙያተኛ ባለቤት ሆኖ ሊሠራ ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶክተር) ገለጹ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠና ማዕከል ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጋር በመተባበር "ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና" በሚል ርዕሰ ጉዳይ ባዘጋጀው ሥልጠና ላይ አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም ጽሑፍ አቅርበዋል።

በወቅቱ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የአደጋ ስጋት አመራር ሥራዎች ላይ በሀገሪቷ የሚገኙ የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያዎች ባለቤት ሆነው መሥራት እንደሚገባቸው ተናግረዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ የአደጋ ስጋት አመራር የአንድ ተቋም ብቻ ኃላፊነት ሳይሆን ሁሉም ተቋማት በጋራ ኃላፊነት ወስደው የሚያከናውኑት ሥራ ነው።

የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያው በሀገሪቷ በሚያጋጥሙ የአደጋ ስጋት አመራር ጉዳዮች ባለቤት ነው። የአደጋ ስጋት ግንዛቤን ማጎልበት፣ የዝግጁነት ጉዳይ ምላሽና የማገገም እንዲሁም መልሶ ማቋቋም ሥራዎችን በኮሙኒኬሽን ሥራዎች እየተነተኑ ማቅረብ ያስፈልጋል ብለዋል።

ስለአደጋ ስጋት አመራር ኮሚዩኒኬት ስናደርግ ከአደጋ በፊት፣ በአደጋ ወቅትና ከአደጋው በኋላ ያለውን ሁኔታ ማየት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ድርቅን በተመለከተ ከኮሙኒኬሽን አንጻር አደጋውን በየደረጃው ማሳየትና ድርቁ ሰብዓዊ ቀውስ እንዳያስከትል መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ድርቅ ቀድሞ በ100 ዓመቱ ይከሰት ነበር፤ ቀጥሎ በየ10 ዓመቱ፤ አሁን ላይ ደግሞ በየ5 ዓመቱ እራሱን እየደገመ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ረጂዎች በአንጻሩ እሳት ማጥፋት ላይ እንጂ በዘላቂ መፍትሔው ላይ እንደማያተኩሩ አስረድተዋል።

ሁኔታው ከመከላከል ባለፈ ለመልካም አጋጣሚ በሚውሉ ጉዳዮች ላይ ዘላቂ ሥራዎች እንዲከናወኑ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ አምባሳደር ሽፈራው ገልጸዋል።

ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን የተረጂነት ስሜት ደረጃ በደረጃ ለማቃለልና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መከናወን አለባቸው ብለዋል፡፡

ከቤተሰብ አንስቶ እስከ ከፍተኛ ተቋማት ድረስ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ሥራዎችን በኃላፊነት መሥራት ይገባል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያው የአደጋ ስጋት አደጋዎች በደህንነት፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያ መስተጋብሮች ላይ የበለጠ ጫና እንዳያደርሱ መሥራት እንዳለባቸው ገልጸዋል።

በሥልጠናው ላይ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤክስፐርት የሆኑት ማክልዳ ጀቫኒ የማኅበራዊ ሚዲያ ደህንነት /social Media Security/ በተሰኘ ርዕስ ሥልጠና ሰጥተዋል።

በሥልጠናው ተገቢውን መረጃ ከማስተላለፍ ጎን ለጎን ከሃከሮች /መረጃ መንታፊዎች/ የሳይበር ደህንነት ጥቃት እራስን መከላከል የሚቻልባቸው መንገዶች ላይ አተኩሮ መሥራት እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያውን አቅም መገንባት የቻለ ሥልጠና ተሰጥቷል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጋር በመተባበር ባዘጋጀው መድረክ የኮሙኒኬሽን አመራርና ሙያተኛውን አቅም መገንባት የቻለ ሥልጠና ተሰጥቷል ሲሉ የክልልና የፌዴራል ተቋማት ኮሙኒኬሽን ኃላፊዎች ገለጹ።

"ውጤታማ ተግባቦት ለኢትዮጵያ ልዕልና" በተሰኘው የኮሙኒኬሽን ሥልጠና ከመጋቢት 30 ቀን እስከ ሚያዚያ 3 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ለአራት ቀናት በአዳማ ከተማ ተካሂዷል።

በሥልጠናው የተሳተፉት የሲዳማ ክልል ፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊ አቶ ፊሊጶስ ናሆም፤ ለኮሙኒኬሽኝን አመራርና ባለሙያዎች የቀረበው ሥልጠና ሀገራዊ እሳቤ ላይ ያተኮረና ሙያዊ ክህሎትን የሚያዳብር በመሆኑ ለቀጣይ ሥራዎች መሻሻል የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢፕድ ያቀረበው ሥልጠና የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን ውጤታማነት የሚያሳድግ ፤ በውይይትና በተግባር የታጀበ በመሆኑ ውጤታማ ቆይታ ነበረን ሲሉ ገልጸዋል።

"የሥልጠና መርሐ ግብር ላይ የቀረቡ ጽሑፎችና የሥልጠና ሃሳቦች የኮሙኒኬሽን ባለሙያውን አቅም በመገንባት ረገድ ላቅ ያለ ሚና የሚጫወቱ ናቸው። ኢፕድ ጥራት ያለው ሥልጠና ማቅረቡ የሚያስመሰግነው ነው" ብለዋል።

የአፋር ክልል ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሐዋ አሊ አቡበከር በበኩላቸው፤ ኢፕድ የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያው በዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴው ውስጥ ውጤታማና ተቀባይነት ያለው ሥራ ማከናወን የሚያስችለውን አቅም የገነባ ሥልጠና ማቅረቡን ተናግረዋል።

ዘርፉን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ሀገራዊ እሳቤ ላይ ይበልጥ ማተኮርና ተቀናጅቶ መሥራት እንደሚገባ በሥልጠናው መገለጹን ጠቁመው፤ በአጠቀላይ ስልጠናው የኮሙኒኬሽን ክህሎትና የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን የሚያሳድጉ ጠቃሚ ጉዳዮች የተገኙበት መሆኑን ገልጸዋል።

ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ እንደገለጹት፤ ኢፕድ የክልል የዞንና የወረዳ መዋቅሮች ውስጥ ለሚገኙ የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች ተመሳሳይ ሥልጠናዎችን ማቅረብ ቢችል እንደሀገር ያለውን የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ውጤታማነት ማሳደግ ይቻላል።

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ አቶ ጄይላን አብዲ በበኩላቸው ኢፕድ ያቀረበው የኮሙኒኬሽን ሥልጠና ለሥራቸው ትልቅ አቅምን የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል።

በተቋማት መካከል የተቀናጀ የኮሙኒኬሽን ሥራ ለማከናወንና ሀገራዊ እሳቤን የያዙ የተግባቦት ሥራዎችን ለማጠናከር የሚረዳ ስልጠና እንደተሰጣቸው ገልጸዋል።

በኮሙኒኬሽን ዘርፉ ያለውን የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን ለማሳደግ የሚረዳ በተግባርና በውይይት የታገዘ ሥልጠና መሆኑን አቶ ጄይላን ጠቁመዋል።

የጤና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና የጤና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ተገኔ ረጋሳ (ዶክተር) በበኩላቸው፤ኢፕድ የተቋማትን ተግባቦት ሥራዎች አቅም ማሳደግ የሚያስችል ውጤታማ ሥልጠና አቅርቧል ሲሉ ተናግረዋል።

ኮሙኒኬሽን በፕሮፌሽኑ መሠረት መመራት ያለበት ዘርፍ ነው ያሉት ዶክተር ተገኔ፤ ሥልጠናው ሳይንሳዊና በተግባር ክንውን የታጀበ ውጤታማ የኮሙኒኬሽን ሥራዎች ላይ ያተኮረ በመሆኑ ሳቢ ነበር ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

ኅብረተሰቡ ውስጥ በጎ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚረዳ የሥልጠና ይዘት በመሆኑ ሁሉም የኮሙኒኬሽን አመራርና ባለሙያ ጠቃሚ ሃሳቦችን የያዘበት ሥልጠና መሰጠቱን አስታውቀዋል።

ከተለያዩ ክልሎችና ተቋማት የመጡ ሠልጣኞቹ በቀጣይ ለሚያከናውኗቸው የማኅበራዊ ሚዲያ ተሳትፎ፣ በኮሙኒኬሽንና ተግባቦት ሥራዎች ማደግ እንዲሁም በሀገራዊ የልማት ክንውኖች ላይ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚረዳ ግብዓት ማግኘታቸውንም ገልጸዋል።



ሃዊ ዓሊ



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ፊልጶስ ናሆም



ዶክተር ተገኔ ረጋሳ

# ዞኑ ለደንና ለምግብነት የሚውሉ ችግኞችን እያዘጋጀ ነው

## • 38 ሺህ 774 የአቡካዶ ችግኝ ተዘጋጅቷል

**ገመቹ ከድር**

አርሲ ፡- ለዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ለደንና ለምግብነት የሚውሉ ችግኞችን አዳቅሎ በማዘጋጀት ላይ እንደሚገኝ የአርሲ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡ ለደንና ለምግብነት የሚውሉ ችግኞችን በማዳቀል ዝርያቸውን በማሻሻልና ለውጪ ገበያ የሚውሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ በትኩረት እየሠራ መሆኑንም ጠቁሟል፡፡

የአርሲ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት የአትክልት፣ ፍራፍሬ እና ቅመማ ቅመም ዘርፍ ኃላፊ አቶ አሥራት ካሣዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ በ2015 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ ልማት ለደንና ምግብነት የሚውሉ ችግኞች በሄጦሳ ወረዳ በሻቅ ሸረራ ችግኝ ጣቢያ እየተዳቀሉ ይገኛሉ ፡፡

በዞኑ 54ሺ የአቡካዶ ችግኞችን ለማዳቀል እየተሠራ ሲሆን እስከ አሁን ድረስ በተሠራው ሥራ 38 ሺህ 774 የአቡካዶ ችግኝ ማዳቀል መቻሉን ኃላፊው ጠቁመው፤ከነዚህም ውስጥ 13ሺ 500 በሻቅ ሸረራ ችግኝ ጣቢያ የተዳቀሉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ አሥራት ገለጻ፤ ችግኞችን አዳቅሎ ዘራቸውን ማሻሻል የችግኞች በሽታን የመቋቋም አቅም በመጨመር ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ በችግኝ ጣቢያው ተዳቅሎ ዝርያው እየተሻሻለ የሚገኘው አቡካዶ ዝርያ የዘር መስጫ ጊዜውን ከስምንት ወደ ሦስት ዓመት ማሳጣር እንደሚቻል እንደምሳሌነት አንስተዋል ፡፡

መንግሥት የዘረጋው የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንሼቲቭ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ችግኞችን ማዳቀል አስፈላጊነቱ የጎላ ነው ያሉት አቶ አሥራት፤



የማዳቀል ሥራ በሻቃ ሸረራ ችግኝ ጣቢያ

ዲሽጣ፣ ማንጎ፣ ቴምር እና ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ዝሪያዎችን በክላስተር በማምረት ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ አትክልትና ፍራፍሬ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

በበጀት ዓመቱ ብቻ በዞኑ በሰባት ሺህ ሄክታር ላይ ከለማው የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻ፤ አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ለመሰብሰብ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው እስከ አሁን ድረስ 600 ሺህ ኩንታል የተለያዩ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ተሰብስቧል ብለዋል፡፡

ዞኑ በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንሼቲቭ 12 የአትክልትና ፍራፍሬ ዝርያዎችን በክላስተር ማምረት ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ እንደሚሠራበት ገልጸዋል፡፡

የአርሲ ዞን ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ገና መሐመድ በበኩላቸው በዞኑ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የአረንጓዴ አሻራ ልማት ሥራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው ብለዋል፡፡ በ2015 ዓ.ም 254ሺህ ችግኞች ለመትከል ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው እስከአሁን በተሠራው ሥራ 210 ችግኞች በችግኝ ጣቢያ መዘጋጀት መቻሉን ገልጸዋል ፡፡

ከዚህ በፊት በተሠራው የአረንጓዴ አሻራ ልማት ከዚህ በፊት የወደሙ ደኖች ወደ ቦታቸው በመመለሳቸው አርሶ አደሩ ንብ በማነብ ለማር ምርት እና ለእንስሳት መኖ እየተጠቀመበት መሆኑን ገልጸው ዞኑ የተጀመረውን ልማት ዘላቂ ለማድረግ በ249 ሺህ ሄክታር አፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ማከናወኑን ጠቁመዋል፡፡

ሄጦሳ ወረዳ ሻቃ ሸረራ ችግኝ ልማት ጣቢያ ተቆጣጣሪ አቶ ድሪባ ገነና ጣቢያው በ2015 ዓ.ም የሚተከሉ ከ800 ሺህ በላይ ችግኞችን እያዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ችግኞቹም በሐምሌ ወር እንደሚሰራጩ ገልጸው በጣቢያው የተለያዩ የአትክልትና ፍራፍሬ ዝርያዎችና ለደን አገልግሎት የሚውሉ እንደ ግራቪያ፣ዝግባ እና ሌሎችም ችግኞች በጣቢያው መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል፡፡

ዜና

# መልካም ስብዕና ያላቸውን ወጣቶች ለመቅረጽ ልዩ ትኩረት መስጠት ይገባል

**መዓዛ ማሞ**


ፎቶ፡- እዮብ ተፈራ

አዲስ አበባ፡- ለወጣቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት እና ምቹ ሁኔታን በመፍጠር መልካም ስብዕናቸውን መቅረጽ ካልተቻለ ወደ ጥፋት እና አፍራሽ ተግባር የመግባት ዕድላቸው የሰፋ መሆኑን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ገለጹ፡፡

ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ትናንት በተካሄደው የፀረ አደንዛዥ ዕፆች ሀገር አቀፍ የንቅናቄ ማስጀመሪያ ፕሮግራም ላይ ተገኝተው ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለጹት፤ ወጣቶች ያላቸውን አቅም ፤አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠርና ለውጥን የማምጣት ችሎታ ለመጠቀም በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ዘላቂ ልማት ፤ሰላም እና ዲሞክራሲ ለማረጋገጥ ዛሬ ላይ ለወጣቶች የሚሰጠው ትኩረትና የሚፈሰው መዋለ ንዋይ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በሀገራችን ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ወጣቶች ዕምቅ አቅም፣ብሩህ አዕምሮ ፤የምርምር እና ፈጠራ ዝንባሌ ያላቸው አምራች ኃይል በመሆናቸው ለሀገር እድገት እና ብልጽግና የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ እጅግ የላቀ እንደሆነ የተናገሩት ሚኒስትሯ፤ ለእነዚህ ወጣቶች በቂ ትኩረት ካልተሰጠ እና ስብዕናቸውን በተገቢው ሁኔታ መቅረጽ ካልተቻለ በቀላሉ ለችግር በመጋለጥ ወደ ጥፋት እና አፍራሽ ተግባር የመግባት እድላቸው የሰፋ ነው ብለዋል፡፡

ትናንት በይፋ የተጀመረው ሀገር አቀፍ የንቅናቄ ፕሮግራሙ የፀረ አደንዛዥ ዕፆች እና አሉታዊ መጤ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል እንዲሁም የወጣቶችን ስብዕና እና ሥነ ምግባር በመገንባት ረገድ የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሠራሮችን ለማጠናከር የበኩሉን እገዛ እንደሚያደርግም ጠቁመዋል፡፡


ንቅናቄው "ወጣቶችን ከአደንዛዥ ዕፆች እና አሉታዊ መጤ ልማዳዊ ድርጊቶች እንታደግ!" በሚል መሪ ቃል የሚደረግ ሲሆን ከሚያዚያ 2015- ሚያዚያ 2016 ለአንድ ዓመት የሚቆይ መሆኑም ተገልጿል፡፡

በመድረኩ በአደገኛ ዕጾችና አሉታዊ መጤ ልማዳዊ ድርጊቶች መከላከል ላይ የንቅናቄ ማስጀመሪያ መነሻ ጽሑፍ ያቀረቡት በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ማብቃት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ባንቹ ሙሉጌታ እንደገለጹት ፤የንቅናቄው አስፈላጊነት አደንዛዥ ዕፆች በወጣቶች ስብዕና ላይ እያስከተሉ ያለውን መጠነ ሰፊ አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተደራጀ፣ በተቀናጀና ቀጣይነት ባለው መልኩ በትኩረት እንዲሠሩ ለማድረግ መሆኑ ተገልጿል።

በንቅናቄው ዩኒቨርሲቲዎች ፣ የሚዲያ አካላት እና ባለ ድርሻ አካላት እንደተሳተፉ ተገልጿል፡፡

አደንዛዥ ዕጾች በወጣቶች ስብዕና ላይ የሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ ላይ የሚያተኩር ጥናታዊ ጽሑፍ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ አዕምሮ ሕክምና መምህር እና ተመራማሪ በሆኑት በፕሮፌሰር ሰለሞን ተፈራ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

በማስጀመሪያ ፕሮግራሙ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች ተወካዮች፣ የክልል ቢሮ ኃላፊዎች፣የወጣቶች ተወካዮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል፡፡



# ለመጪዎቹ በዓላት በቂ የእርድ ከብቶች መቅረባቸው ተገለጸ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ለመጪዎቹ በዓላት የሚያስፈልገውን የእርድ ሥራ ለማከናወን በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረጉን አስታወቀ:: ለበዓላቱ በቂ የቁም እንስሳት መቅረባቸውም ተጠቁሟል::

የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ከአዲስ አበባ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማኅበር እና ከአዲስ አበባ ሉካንዳ ነጋዴዎች ማኅበር ጋር በመሆን በትናንትናው ዕለት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል::

የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ማኔጅመንት ዳይሬክተር አቶ ሰኢድ ኢድሪስ በሰጡት መግለጫ፤ ባለፉት 55 ቀናት ድርጅቱ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል:: በዚህም ለበዓሉ የሥጋ ማሰራጫ የሚሆኑ 43 መኪናዎች እና ጊዜያዊ በረቶች ተዘጋጅቷል::

በፋሲካ በዓል የእርድ ቁጥሩ ስለሚጨምርና ለኅብረተሰቡ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ታልሞ 250 ጊዜያዊ ሠራተኞች መቀጠራቸውን ያስታወቁት ኃላፊው፤ ለበዓሉ የሚያስፈልገውን ዝግጅት ማጠናቀቁን እና ለመጪው ፋሲካ በዓል ሁለት ሺህ 500 የዳልጋ ከብቶች እና ከሦስት ሺህ እስከ አራት ሺህ በግና ፍየል ይቀርባል ሲሉ አብራርተዋል::

እንደ አቶ ሰኢድ ገለጻ፤ ዋጋን በተመለከተ የበግና የፍየል ሥጋ በኪሎ 400 ብር እንዲሁም የበሬ ሥጋ በኪሎ 500 ዋጋ ወቶላቸዋል:: በዚህ ዋጋም ኅብረተሰቡ የተመረመረ እና ሁሉ ነገር ያለቀለት ሥጋ ማግኘት ይችላል::

እርዱ እንዳይዘገይ ከግብዓትም ሆነ ከሰው ኃይል ጀምሮ በተቻለ መጠን አስፈላጊውን ሁሉ በተቋሙ አሟልተናል ያሉት አቶ ሰኢድ ለበዓሉ በግም ሆነ በሬ በቄራዎች አገልግሎት አምጥቶ መጠቀም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አገልግሎቱን ማግኘት የሚችልበትን ሁኔታ አመቻችተናል ብለዋል:: ሕገወጥ እርድን ኅብረተሰቡ ተባብሮ ማስቀረት መቻል አለበት ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል::

የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ መዓዛ ቀለመወርቅ በበኩላቸው፤ማኅበሩ አቅርቦትን አስመልክቶ ብዙ ዝግጅቶችን አድርጓል:: በዚህም ከዛሬ ጀምሮ ከሁሉም ክልሎች እንስሳቱ መግባት ይጀምራሉ::

የእንስሳት እጥረት እና የዋጋ ንረት እንዳይፈጠር ከተለያዩ ክልሎች ጋር በመነጋገር ብዙ ቅድመ ዝግጅት ሲደረግ መቆየቱንም ወይዘሮ መዓዛ አብራርተዋል::

የአዲስ አበባ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ትዕግስት በዳዳ እንደገለጹት፣ የቀጣይ የፋሲካ እና የኢድ አልፈጥር በዓልን መሠረት አድርጎ ለሚከሰቱ ምግብን ከባዕድ ጋር ቀላቅሎ የመሸጥ ሕገወጥ ሥራዎችን ለመቆጣጠር የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተው የዘመቻ ሥራ እየተሠራ ይገኛል::

በዚህም በብዛት ለበዓል የሚፈለጉ የታሸጉም ሆኑ ያልታሸጉ ምግቦች፣በከተማ ውስጥ ያሉ ሉካንዳ ቤቶች፣ ለፀሐይ የተጋለጡ ምግቦች እና መጠጦች እንዲሁም ትንባሆና አደንዛዥ እጽ ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሠራ ይሆናል ብለዋል::

የአዲስ አበባ ሉካንዳ ነጋዴዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አየለ ሳሕሌ በበኩላቸው፤ በዓሉን አስመልክቶ ሁሉም አባላት ለሁለት ወር ዝግ ሆኖ የነበረው የሥራ ቦታቸውን የማጽዳት ሥራ እየሠሩ ቆይተዋል ያሉ ሲሆን ግብይቱ የሚከናወነው ከዚህ በኋላ ባሉት ቀናት በመሆኑ የሥራ ዝግጅቱን መጨረሳቸውን አመላክተዋል::

# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በመጪዎቹ ሁለት ዓመታት ከስድስት በመቶ በላይ ዕድገት ያስመዘግባል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- እ.አ.አ. በ 2023ና 2024 የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት የስድስት ነጥብ አንድ እና ስድስት ነጥብ አራት በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (አይኤምኤፍ) አስታወቀ፡፡

አ ይ ኤ ም ኤ ፍ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ መሠረት አድርጎ ባወጣው ሪፖርት እንደገለጸው፤ በኢትዮጵያ ተከስተው የነበሩ ግጭቶች በ መ ቀ ነ ሳ ቸ ው ና በአፍሪካ ፈጣን ዕድገት ለማስመዝገብ የታለመው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ጥረት ቀጣይነት ባለው መልኩ እየተከናወነ በመሆኑ ኢኮኖሚው ዕድገት እንደሚያሳይ ይጠበቃል።

እ.አ.አ. በ2023 ኢትዮጵያ ከሰሐራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት መካከል በኢኮኖሚ ዕድገቷ አራተኛ ደረጃ ላይ እንደሆነች አይኤምኤፍ አስታውቋል፡፡

እንደ አይኤምኤፍ ገለጻ፤ እ.አ.አ. በ2023 ከሰሐራ በታች ካሉ ሃገራት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ከሚያስመዘግቡት ሀገራት መካከል ሴኔጋል የስምንት ነጥብ ሦስት በመቶ ዕድገት እንደምታስመዘግብ ተገምቷል።

ዲሞክራቲክ ኮንጎ በአንጻሩ የስድስት ነጥብ ሦስት በመቶ ዕድገት እንዲሁም አይቮሪኮስት ስድስት ነጥብ ሁለት በመቶ እንደሚያድጉ ይጠበቃል ሲል አይኤምኤፍ ጠቁሟል።

እአአ በ2024 አቆጣጠር ከሰሐራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት በአራተኛና አምስተኛ ደረጃ የተቀመጡት ኢትዮጵያና ኡጋንዳ ደግሞ ኢኮኖሚያቸው በስድስት ነጥብ አንድ በመቶና በአምስት ነጥብ ሰባት በመቶ ዕድገት እንደሚኖራቸው ሪፖርቱ አመላክቷል።

በተጨማሪም እ.አ.አ. በ2023 የኢትዮጵያ ጥቅል ሀገራዊ ምርት /ጂዲፒ/ 126 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር እንደሚደርስ አይኤምኤፍ አስታውቋል።

በአልቫሮ ፒሪስ የሚመራው የአይኤምኤፍ ቡድን እ.አ.አ. ከመጋቢት 27 እስከ ሚያዚያ 7 ቀን 2023 ድረስ በአዲስ አበባ ቆይታ በማድረግ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ ጥናት አድርጓል።

በጉብኝቱ ማጠቃለያ ላይ የቡድኑ ኃላፊ የአይኤምኤፍ ቡድን ቁልፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ተጋላጭነትን ለመፍታት እና የኢትዮጵያን ከፍተኛ የኢኮኖሚ አቅም ለማውጣት ያለመውን የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ ላይ ከኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ጋር ውይይት ማድረጋቸውን አስታውቀዋል።

የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት በተሻለ መጠን ከፍ ማድረግ የሚያስችል አቅም የያዘ በመሆኑ አይኤምኤፍ ድጋፍ እንደሚያደርግ መግለጻቸው የሚታወስ ነው።

# በዓመት ሦስት ሚሊዮን ቶን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በድሬዳዋ የሚገነባው የሲሚንቶ፣ ብረትና ኖራ ፋብሪካ የወቅቱ ፈተና የሆነውን የግንባታ ግብዓቶች እጥረት የሚፈታ እንደሚሆን ያላቸውን ፅኑ ዕምነት የገለጹት ሚኒስትሯ፤ የግንባታ ግብዓቶችን አምራች ኢንዱስትሪዎችን የማበረታታትና የመደገፍ ሥልጣን ለመሥሪያ ቤታቸው መሰጠቱን አንስተዋል፡፡

በዚህም ምርት በብዛት እንዲመረትና ገበያው እንዲዘምን በማድረግ ኃላፊነታችንን እንወጣለን ብለዋል።

የናሽናል ዌስት ኢንተርናሽናል ሆልዲንግ የሀገር ውስጥ የምርት ፍጆታን በመሸፈን የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት የሚችል መሆኑን ጠቁመው፤ ኩባንያው የሥራ ዕድል ከመፍጠር እና የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት ባለፈ የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ የሚያስተዋውቅ መሆኑንም ገልጸዋል።

በዓመት እስከ ሦስት ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ የማምረት አቅም ያለው ይህ ትልቅ ፋብሪካ መገንባቱ በሀገሪቱ እየታየ ያለውን የግንባታ ግብዓት እጥረት ለመፍታት ተስፋ የሚሰጥ መሆኑን ጠቅሰው፤ ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያን ተቀባይ ከመሆን ወደ ሻጭ ሀገር ያሻግራል የሚል እምነት እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡

የኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ ኩባንያ ሊቀ መንበር አቶ ብዟየሁ ታደለ በበኩላቸው፤ አጠቃላይ ግንባታው 540 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚወስድ መሆኑን ጠቅሰው፤ የመጀመሪያ ዙር ግንባታ 243 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ይደረግበታል ብለዋል። የሚገነባው ፋብሪካ ከሲሚንቶ እና ብረት በተጨማሪ የኖራ ምርት እንደሚያመርት ተናግረዋል።

ፋብሪካው 700 ሺህ ቶን ብረት፣ 1000 ቶን ኖራ እና ሦስት ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ በዓመት ማምረት የሚችል መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

የኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ ካምፓኒ አጋር የሆነው የቻይናው ዌስት ኢንተርናሽናል ሆልዲንግ ካምፓኒ ሥራ አስፈፃሚ ሚስተር ዋንግ ፋይን በበኩላቸው፤ ፋብሪካውን በአጭር ጊዜ ሠርቶ ለማጠናቀቅ ጥረት ይደረጋል ያሉ ሲሆን ፋብሪካው ሥራ ሲጀምር በሀገሪቱ ያለውን የሲሚንቶ እጥረት ከመቅረፉም በላይ ለ10 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ብለዋል።

# "ባለውለታ የሆኑ የልዩ ኃይል አባላት እንዲበተኑ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ዶክተር ሰማ ትናንት በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ ለማደራጀት ሲታሰብ የአማራ ክልል መሪዎች ብቻቸውን የወሰኑት አይደለም። ውሳኔው የሀገር ዓርማ የተላበሰ ጠንካራ የመከላከያ ኃይል ለመገንባት ያለመ ነው፡፡

በዚህ የጋራ ውሳኔ መሠረት የአማራ ልዩ ኃይልም ወደ ሀገር መከላከያ ሠራዊትና ፌዴራል ፖሊስ በመቀላቀል የተለመደ የሀገር ዘብነት ተግባሩን እንዲያስቀጥል ተፈልጎ ውሳኔው መወሰኑን አብራርተዋል፡፡

"አንድነቷ የጸና እና የታፈረች ኢትዮጵያን ለመገንባት አንድ ዓይነት የሀገር ዓርማ የተላበሰ ኃይል ያስፈልገናል" ያሉት ዶክተር ሰማ፣ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ በማደራጀት ጠንካራ የሀገር የጸጥታ ኃይል ለመፍጠር የታመነበትን ውሳኔ ለመቀልበስ ውዥንብር የሚፈጥሩ አካላት ስለመኖራቸውም ገልጸዋል።

ውሳኔውን በውል ባለመገንዘብ ከካምፕ የወጡ የልዩ ኃይል አባላትን እውነቱን አሳውቆ የሚያሰባስብ ግብረ ኃይል በክልሉ ሁሉም ወረዳዎች ላይ ተቋቁሞ እየተሠራ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

የአማራ ልዩ ኃይል ክልሉ ብሎም ሀገር ችግር ላይ በወደቀበት ወቅት ከመከላከያ ሠራዊት ጋር በመሆን መስዋዕትነት ከፍሎ ሀገር ያቆመ የታሪክ ባለቤት ስለመሆኑም ገልጸዋል። ልዩ ኃይሉ ውዥንብር የሚፈጥሩ አካላትን አሉባልታ ወደ ጎን በመተው መልሶ ወደ ማደራጀት የላቀ የሀገርንና ሕዝብን ሰላም የማስጠበቅ ተልዕኮ መቀላቀል እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

ዶክተር ሰማ "የልዩ ኃይል አባላት ትጥቃቸውን አስረክበው እንዲበተኑ ሳይኾን የያዙትን ትጥቅ አስመዝግበው ወደላቀ ተልዕኮ እንዲሸጋገሩ ነው የተፈለገው" ብለዋል። ይህም ሲኾን የአማራ ልዩ ኃይል ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር በመኾን የሀገርን ዳር ድንበር ለማስጠበቅ የሚችል ጀግና ኃይል ስለመኾኑ ታምኖበት ነው ብለዋል።

የአማራ ክልልን ሕዝብ ብሎም የሀገርን ሰላም ለማስጠበቅ ከክልል ልዩ ኃይልነት ከፍ በማለት ሀገራዊ የጸጥታ መዋቅሮችን መቀላቀል እንደሚያስፈልግ ለልዩ ኃይል አባላት መልዕክት አስተላልፈዋል።

የተወሰነውን ውሳኔ በውል ባለመረዳት ከሰሞኑ የተፈጠረውን የሕዝብ ስሜት ለማረጋጋት የሃይማኖት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች ያደረጉት አስተዋፅዖ ከፍተኛ እንደነበር ዶክተር ሰማ ጠቅሰዋል። ወጣቶች ላሳዩት ስክነት እና ሥልጡንነትም ምስጋና አቅርበዋል።

ዶክተር ሰማ ወደ አላስፈላጊ የሰላም መደፍረስ ከመግባት በፊት ውይይቶችን ማድረግ እና መግባባት መቻል መልካም መሆኑን ተናግረዋል።

አሁን ያለውን ድባብ ሙሉ በሙሉ ወደ ሰላም በመቀየር በቀጣይ የሚከበሩ የክርስትና እና የእስልምና በዓላትን በሰላምና በፍቅር ማሳለፍ እንደሚገባም መልዕክት አስተላልፈዋል።



ዘመን ባስ ኢትዮጵያ ትራንስፖርት አገልግሎት
Zemen Bus Ethiopia Transport Service

ለክቡራን መንገደኞቻችን እና ለመላው ኢትዮጵያውያን እንኳን ለትንሳኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያልን በዓሉ የሰላም እና የደስታ እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞታችንን እንገልጻለን፡፡
በማንኛውም ጊዜ ወደ ሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል ጉዞ ለማድረግ ሲያስቡ ዘመን ባስ ይሁን ምርጫዎ ትኬትዎን ለመቁረጥ እና መረጃ ለማግኘት በአጭር ስልክ ቁጥር 6162 አሁኑኑ ይደውሉ

መልካም በዓል!




ዘመን ባስ
በምቾት የሚያደርስ

## የጨረታ ማስታወቂያ

የደ/ብ/ብ/ሕ/መንግስት በጋሞ ዞን አርባምንጭ አጠቃላይ ሆስፒታል በ2015 በጀት ዓመት

1/ ለተኝቶ ታካሚ ሕሙማን የበሰለ ምግብ ማቅረብ የሚችል ድርጅቶችን በጨረታ አወዳድሮ በየሰድስት ወሩ የጥራት ሁኔታው ተረጋገጦ ውል እየታደሰ ለማሰራት ይፈልጋል፡፡

**ስለዚህ በጨረታው ለመካፈል የሚፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች በተገለጸዉ መስፈርት መሠረት ቀርበው መወዳደር ይችላሉ:**

1. ተጫራቾች በዘርፉ ህጋዊ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የግብር ከፋይነት ሰርተፊኬት Tin number/ ማቅረብ የሚችሉ ሆነው ዓመታዊ የሥራ ግብር የከፈሉበትን በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና መረጃ ሰነዶቻቸውን ኦሪጂናልና ኮፒ በተለያየ ፖስታ ካሸጉ በኋላ በአንድ እናት ፖስታ በማሸግ ከጨረታ ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. የጨረታው ማስከበሪያ 30,000. /ሰላሣ ሺህ/ ብር በባንክ በተረጋገጠ ክፍያ ማዘዣ (CPO) ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ አለባቸው፡፡
3. የጨረታው ዶክመንት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ በመደበኛ የሥራ ቀናት የማይመለስ ብር 200 /ሁለት መቶ/ ብር ከሆስፒታላችን ግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ቢሮ በመቅረብና በመክፈል የጨረታውን ሰነድ መውሰድ ይችላሉ
4. የተጫራቾች ካፒታል መጠን ቢያንስ 200,000 ብር በላይ በባንክ ስለመኖሩ የባንክ ስቴትሜንት መረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ ቫትን ብቻ ያካተተ ሆኖ አሸናፊው የሚለየው በአጠቃላይ ድምር ዋጋ ዝቅተኛ ያቀረበ ይሆናል
6. የጨረታው ዶክመንት በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ አድራሻውን በመጻፍ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ 15 ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ሲሆን በ16ኛው የሥራ ቀን 3.30 - 4:00 ሰዓት ባለው በሆስፒታላችን ግ/ፋ/ን/አስተዳደር ክፍል ለዚህ አገልግሎት በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡
7. የምግብ አቅራቢ ተጫራቾች ለሥራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በግላቸው ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው::
8. ጨረታዉ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ዉክሎቻቸዉ ባሉበት ከላይ በተጠቀሰዉ ቀንና ቦታ ከቀኑ በ16ኛው ሥራ ቀን በ9.00 ሰዓት ላይ ይከፈታል ::
9. ሆስፒታሉ የተሻለ መንገድ ካገኘ በጨረታው አይገደድም::

**ተጨማሪ ማብራሪያ ፡-**

**በስልክ ቁጥር 0468810839 /0934706781 በመደወል ማግኘት ይችላሉ:**

**በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መን/ በጋሞ ዞን የአርባምንጭ አጠቃላይ ሆስፒታል**

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሪፎርሙ ልዩ ኃይሉን ስላቀ ድል የሚያበቃ ነው!

በአንድ አገር ዘላቂ ሰላም ማስፈን የሚቻለው ጠንካራ የመከላከያና የፀጥታ ተቋሞችን በአስተማማኝ ሁኔታ መገንባት ሲቻል ብቻ ነው። በተለይም ባለንበት ዘመን አገራት በአካባቢያዊ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸውን ተደማጭነት ለማሳደግ በእነዚህ ተቋማት ላይ ከፍተኛ መዋዕለነዋዮችን እየመደቡ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ አቅማቸውን ሲገነቡ ይስተዋላል።

በተለይም ቀጣይ ዕጣ ፈንታቸው ብሩህ ሆኖ የሚታያቸው፣ ለዚህም ብዙ ተስፋ ሰንቀው እየተንቀሳቀሱ ያሉ አገሮች፤ ዘላቂ ሰላምን ዋነኛ አጀንዳቸው በማድረግ ለመከላከያና ለፀጥታ ተቋሞቻቸው ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ይሠራሉ። በሚያስመዘገቡት ስኬት ልክም ሰላማቸውን በማስጠበቅ የሕዝባቸውን የመልማት ፍላጎት እውን ማድረግ እየቻሉ ነው።

በእኛም አገር ለዘመናት ሲንከባለል የመጣውን የሕዝባችንን የመልማት ፍላጎት እውን ለማድረግ፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ አገራዊ የፖለቲካ ባህሉን (የሴራ ፖለቲካ) ከመቀየር ጀምሮ፤ ለውጡ ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲጓዝ በመንግሥት በኩል ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል። ሰላምን እንደ አንድ ዋነኛ የፖለቲካ እሴት ከመስበክ ጀምሮ ስለ ሰላምም ብዙ ዋጋ ከፍሏል።

ከዚህም ጎን ለጎን መንግሥት አገራዊ የለውጥ አስተሳሰቡን መሬት ለማውረድ የሚያስችሉ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በስፋት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። ከዚህም ውስጥ በዋነኝነት በመከላከያና በፀጥታ ተቋሞቻችን ላይ የጀመራቸው የሪፎርም ሥራዎችና እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶች በዋነኝነት ተጠቃሽ ናቸው።

እንደ አገር ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለጀመርነው እልህ አስጨራሽ ትግል አቅም እንደሚሆን የሚታመነው ይህ በመከላከያና በፀጥታ ተቋሞቻችን ላይ የጀመርነው የሪፎርም ሥራ፤ ዕለት ተዕለት አቅሙን እያገዘፈ አገርን ከየትኛውም የህልውና ስጋት መታደግ በሚያስችል ቁመና ላይ እንደሚገኝ፤ የተቋማቱ አመራሮች በብዙ መተማመን የሚናገሩት እውነት ከሆነ ውሎ አድሯል።

ተቋማቱን በተልእኮ በአዲስ መልክ በመግራት ሕዝባዊነታቸውን በጠንካራ መሠረት ላይ ማነጽን፤ የሰው ኃይልና የትጥቅ አቅማቸውን በማዘመን ወቅቱን የሚመጥን ማድረግን ያካተተው የሪፎርም ሥራው፤ ተቋማቱ በርግጥም ትናንት ከነበሩበት አገርን የማይመጥን ቁመና ወጥተው እንደአገር ትልቁን ሕገመንግሥታዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚያስችላቸውን አቅም እንዲገነቡ እያስቻላቸው ነው።

የክልል ልዩ ኃይሎችን በአዲስ መልክ የማደራጀቱ ውሳኔና የማስፈጸም ሂደት የዚህ ሪፎርሙ አካል የነበረና በተለያዩ ውስጣዊ ምክንያቶች የዘገየ ነው። ዋንኛ ዓላማውም ይህንን ኃይል የተሻለ ቁመና በማላበስ አገራዊ አቅም ሆኖ እንዲወጣ ማስቻል ነው።

የክልል ልዩ ኃይል አገር በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በነበረችባቸው ወቅቶች ለሕይወቱ ሳይሳሳ ስለአገሩ የሞተ እና የቆሰለ በዚህም ደማቅ ታሪክ መጻፍ የቻለ ነው። አገሩን በታማኝነት ለማገልገል በእሳት የተፈተነ ማንነት የገነባ፣ ይህ ማንነቱ በየትኛውም ሁኔታ እና አሉባል,ታ የማይፈታ፤ በቀጣይም እየተፈተነ የሚጠራ ነው።

ይህንን ኃይል በተራ አሉባልታ በማደናገር በሞት የተፈተነውንና ጠርቶ የወጣውን የአገር ፍቅሩን ማራከስ የሚቻል አይሆንም። ይህ ኃይል መቼም ቢሆን በጽንፈኞችና ሁከት ጠማቂዎች አጀንዳ ተጠልፎ በሕይወቱ ተወራርዶ በታደጋት አገሩ ላይ የሚነሳ አይሆንም። ለዚህ የሚሆን ማንነት የለውም፤ መቼም ቢሆን ሊኖረው አይችልም።

ከዚህ ይልቅ አሁን እያደረገ እንዳለው የጽንፈኞችንና የሁከት ጠማቂዎች አጀንዳ ረግጦ ራሱን ለላቀ አገራዊ ግዳጅ የሚያበቃበትን የተሻለ ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅበታል። ከዚህ ጎን ለጎንም በጉዳዩ ዙሪያ በሕዝቡ ውስጥ የተፈጠረውን ብዥታ በማጥራት ሂደት ውስጥም ራሱን ግንባር ቀደም አድርጎ ሊንቀሳቀስና የአገር አለኝታነቱን በድጋሚ ሊያረጋግጥ ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ልዩ ኃይልን መልሶ በማደራጀት ዘላቂ ሰላምን ማስፈን

**ዶክተር ጀኔኑስ**

የጦር ኃይሎች ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጄነራል አበባው ታደሰ ከሰሞኑ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ቆይታ አድርገው ነበር፡፡ በዚህም ቆይታቸው በአገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት እና የጸጥታ ተቋማት ላይ እየተደረገ ስላለው ሪፎርም ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። የዚህ ሪፎርም አካል ስለሆነው የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት ሥራም እንዲሁ አንስተዋል።

በማብራሪያቸው በአገሪቱ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ የዳሰሱ ብዙ ጉዳዮችን አንስተዋል፡፡ እሳቸው ከሰጡት ማብራሪያ በመነሳትም አገራችን አሁን ያለችበትን ሁኔታ በተሻለ መልኩ ለመረዳት ችያለሁ። በአንዳንድ ጉዳዮችም ላይ የጠራ ግንዛቤ መጨበጥ የቻልኩ ይመስለኛል።

ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ የሪፎርም አስፈላጊነት በተነተኑበት ማብራሪያቸው፤ አገሪቷ ሁለት ስጋቶች አሉባት፡፡ አንደኛው በምሥራቅ አፍሪካ ያለው ስጋት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በየጊዜው እየተቀያየረ የመጣው የዓለም ሁኔታ በኢትዮጵያ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ነው።

ይህንን አደጋ መመከት የሚቻለው የመከላከያና የጸጥታ ተቋማት ላይ ቀጣይነት ያለው የማያቋርጥ ሪፎርም ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ ይህንን በአግባቡ ለማከናወን ደግሞ ቀድሞ የራስን ቤት ማጽዳት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የትኛውም የሪፎርም ሥራ ብዙ ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥሙት ለመረዳት አያስቸግርም፤ ሪፎርም ይዞት የሚመጣው የለውጥና የመለወጥ ሀሳብ በራሱ ለተግዳሮት የተጋለጠ ነው። በሂደት የመጥራታቸው እውነታ እንዳለ ሆኖ ወደ መሬት ሲወርድም እንቅፋቶች ሊያጋጥሙት ይችላሉ።

በርግጥ በየትኛውም ምክንያት የታጠቀ ኃይል ወጥ በሆነ ማዕከላዊ ዕዝ ስር ካልተዋቀረ ለአገር አንድነት ለሕዝቦች ሰላምና ደህንነት ፈተና አይሆንም ብሎ ማሰብ በየዋህነት ብቻ የሚገለጽ አይደለም። ብሔራዊ አደጋን በአግባቡ ያለማጤን ትልቅ ፈተናን አቅልሎ ማየት ጭምር ነው። ይህ ደግሞ የቱን ያህል ዋጋ ሊያስከፍ እንደሚችል በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል ከተካሄደው ጦርነት በላይ ማሳያ ሊሆን የሚችል ሌላ አንዳች ነገር አይኖርም።

በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመች አገር ለመመስረት ጠንካራ የመከላከያ እና የጸጥታ ሰራዊት መገንባት ወሳኝ ነው። የትኛውም አገር ይህንን እውነታ ታሳቢ በማድረግ በእነዚህ ተቋማት ላይ የማያቋርጥ የሪፎርም ሥራዎችን ይሠራሉ። በእኛም አገር ከለውጡ ማግስት ጀምሮ እየሆነ ያለው ይኸው ነው።

አገሪቱን እንደ አገር በጠንካራ መሠረት ላይ ማቆም የሚያስችል አሻጋሪ ተቋማትን መፍጠር ሲቻል ነው። ይህ ደግሞ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ነው፤ ይህ የተቋማት ሪፎርም ነው ዛሬ ላይ አገርን ከብዙ ፈተናዎች ታድጎ፤ ብዙ ሲሟረትባት ከነበረችበት ሟርትና የጥፋት ድግሶች ወጥታ ጸንታ መቆም ያስቻለው።

በየትኛውም አገር ተሞክሮ መረዳት እንደሚቻለው፤ መሣሪያ ታጥቆ መንቀሳቀስ የሚችለው የሕግ ድጋፍ ያለው አካል ብቻ ነው፤ የመከላከያ እና የጸጥታ ተቋማት። በአንድ አገር ውስጥ ከእነዚህ ውጪ የታጠቀ ኃይል የመኖሩ ጉዳይ አገሪቱን ለተለያዩ ስጋቶችና ተጨባጭ አደጋዎች መጋበዙ የማይቀር ነው።

በእኛም አገር በተለይ ከክልል ኃይሎች ጋር በተያያዘ የነበረው እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም። ይህ ኃይል አገሪቱ በአስቸጋሪ የህልውና ስጋት ውስጥ በነበረችበት ወቅት የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል በደሙ ታሪክ የጻፈ ኃይል ነው። በዚህም በመላው ሕዝባችን ትልቅ ከበሬታና እውቅና የተቸረው ነው።

ይህም ሆኖ ግን ከተደራጀበት መንገድና የሕግ ድጋፍ የሌለው ከመሆኑ አንጻር፤ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል በመንግሥት በኩል በአዲስ መልክ የሚደራጅበትና በተሻለ ተልዕኮና የማስፈጸም አቅም ወደ ሥራ የሚገባበት ሁኔታ እየተመቻቸ ነው።

በአገራችን ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ማስፈን መቻል የጀመርነውን ልማት በሚፈለገው ፍጥነት እና ጊዜ ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ አቅም ነው። ይህን እውን ለማድረግ ደግሞ በመከላከያና በጸጥታ ተቋማት ላይ የተጀመረው ሪፎርም ወሳኝ ነው።

ይህ ሪፎርም እንደ አገር ያሉብንን ዓለም አቀፍና አካባቢ ስጋቶች በአግባቡ ከመቆጣጠር አንጻር ፋይዳ ያለው፤ ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ከማስጠበቅ አንጻርም እንደ አንድ ትልቅ አቅም ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

ሪፎርሙ ከተጀመረ አንስቶ እየተካሄዱ ያሉ ተግባራት ተቋማቱን በተልዕኮ፣ በሰው ኃይል እና በቴክኖሎጂ በተሻለ መልኩ ለማደራጀት እየተደረገ ያለው ጥረት በብዙ መልኩ ውጤታማ እንደሆነ ይታመናል። አሁን ላይ አገሪቱን ከተለያዩ ስጋቶች መታደግ አስችለዋል፡፡

ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም አበባው ታደሰ በግልጽ ለማሳየት እንደሞከሩት፤ የክልሎች ልዩ ኃይሎች በሙሉ የክልላቸውን ፀጥታ ይጠብቁ ነበር፤ ከመከላከያ ኃይሉ ጋር አብረው ቆስለዋል፤ ደምተዋል፤ ሞተዋል። ይህ ኃይል ይህንን የመሰለ ትልቅ ማንነት አለው።

ለእነዚህ ኃይሎች ደግሞ ሕገመንግሥቱ እውቅና አይሰጣቸውም። እውቅና የሚሰጠው አንደኛ ለመከላከያ፤ ሁለተኛ ለፌዴራል ፖሊስ፤ ሦስተኛ ደግሞ ለክልል መደበኛ ፖሊስ ብቻ ነው። ከዚህ የተነሳም ሕጋዊ መስመር መያዝ አለበት። ወደ ሕጋዊ መስመር እንዲገባ መደረግ አለበት።

ሌላው ችግር የልዩ ኃይሉ አገነባብ ብሔር ተኮር መሆኑ ነው። ብሔር ተኮር ሲባል ኦሮሞው ‹‹ለኦሮሞ ሕዝብ እሞታለሁ›› የሚል፣ የሶማሌው፣ የአፋሩ፣ የአማራው፣ የሲዳማው፣... በተመሳሳይ የሚልበት አካሄድን የሚፈጥር ነው፡፡ ይህ ማለት ‹‹የሌላው ብሔር ጉዳይ ›› ጉዳዬ አይደለም የሚል መንፈስን ስለሚላበስ ሂደቱ የሕዝቦችን አንድነት የሚጎዳ ነው።

ከዚህም በላይ አደረጃጀቱ የአገሪቷን የፖለቲካ መፍቻ መንገድ አበላሽቷል። በእኛ አገር ፖለቲካና ጉልበት የሰጠው ሕገመንግሥቱ በሕዝብ ለተመረጠ መንግሥት ብቻ ነው። ስለዚህ የክልል ልዩ ኃይል ፖለቲከኛው በሀሳብ ማሸነፍ ሲያቅተው ሌላ በትር ዕድል ሰጥቷታል። ሁለት ዓመት ሙሉ በጦርነት የቆየነው በዚህ ምክንያት ነው።

ይህ ኃይል ከዚህ በከፋ መልኩም ለአገርና ለሁሉም ሕዝቦች የሚሞተውን መከላከያ ሰራዊት መገዳደር የቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ደግሞ ከአገርና ከሕዝቦች ሰላምና ደህንነት አንጻር ምን ማለት እንደሆነ ለመገመት አይከብድም።

የመንግሥት ውሳኔ ትልቅና ኃላፊነት የተሞላበት፤ ከልዩ ኃይሉ ጋር ሲነሱ የነበሩና አሁንም የሚነሱ ተገቢ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችል ነው፡፡ በእነዚህ አደረጃጀቶች ውስጥ የነበረው የሰው ኃይል የተሻለ አገራዊ ኃላፊነት ወስዶ ውጤታማ የሚያደርገውን አቅም እንዲላበስ የሚያደርግ ነው። ይህ ሂደት አገራዊ እፎይታን እንጂ ስጋት ሊፈጥር የሚችል አይደለም።

አሁን ላይ የመንግሥትን ውሳኔ በመቃወም ላይ የሚገኙ ኃይሎች፤ የአገርን ሉአላዊነት ጉዳያቸው ያልሆኑ አክራሪ ብሔርተኞች እና ጽንፈኞች ናቸው፡፡ ጩኸታቸውም ግብ ያደረገው የአገሪቱን የመከላከያ እና የጸጥታ ኃይሎች አቅም በመገንባት ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የሚደረገውን አገራዊ ጥረት ለማደናቀፍ ነው።

Website - www.press.et Email - addiszemen@press.et Facebook - Ethiopian Press Agency

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የክልል ልዩ ኃይል አዲስ አደረጃጀትና የትግበራ አቅጣጫ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ወቅታዊ አገራዊ አጀንዳ ከሆኑት ሰሞነኛ ወሬዎች መካከል የክልል ልዩ ኃይ(ሎች)ል ጉዳይ አንዱ ነው። የክልል ልዩ ኃይል አባላትን ወደ ሌሎች የጸጥታ መዋቅር የማስገባት ሥራ በመላ አገሪቱ እየተተገበረ እንዳለ የመንግሥት መግለጫ ከሰሞኑ አሳውቋል። ይሁን እንጂ ይሄንን መግለጫ በተሳሳተ መንገድ በመረዳትና ያልተገባ መልክ በመስጠት በአገር ላይ ችግር ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች በመስተዋል ላይ ናቸው።

የመንግሥትንም ሆነ የክልል መንግሥታት ያወጡትን መግለጫ ብናስተውል ስለአገርና ስለሕዝብ ሉአላዊነት የሚሞግቱ ሆነው ነው የምናገኛቸው። መንግሥት የአገሪቱን ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስጠበቅ ሁሉን ያማከለ አንድ ጠንካራ ሰራዊት በመፍጠር ሂደት ላይ ብዙ ርቀትን መሄዱ የሚታመን ሲሆን ሰሞነኛ መግለጫውም ይህንኑ እውነታ የሚያጠነክር ሆኖ እናገኘዋለን።

በዚህም መሠረት የክልል ልዩ ኃይሎች እንደየፍላጎታቸው ወደ ተለያዩ የጸጥታ መዋቅሮች የሚገቡበት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመተግበር ላይ ይገኛል። በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የልዩ ኃይል አባላት እንደምርጫቸውና ፍላጎታቸው በመከላከያ ሰራዊት አባልነት፣ በፌዴራልና በክልል ፖሊስ አባልነት መካተት የሚችሉ ሲሆን፣ በዚህ ነፃ ምርጫ ውስጥ መካተት የማይፈልጉ የልዩ ኃይል አባላት መብታቸው ተጠብቆ፣ ለመቋቋሚያ የሚሆን ሥራና ድጋፍ ተደርጎላቸው በሲቪልነት ወደ ማህበረሰቡ እንደሚቀላቀሉ መንግሥት በመግለጫው አስታውቋል።

ይህን ትግበራ በሚመለከት መንግሥት ከክልሎች ልዩ ኃይል አመራርና አባላት ጋር በመነጋገር መግባባት ላይ መደረሱ የመግለጫው አንዱ አካል ሲሆን፣ በብዙ ጥናትና በተገኘው ውጤትም ለአንድ ጠንካራ አገርና ሰራዊት ውሳኔው የተሻለ መሆኑ ተገልጿል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የክልል ልዩ ኃይልን በተለያየ የጸጥታ መዋቅሮች ውስጥ የማካተቱ ውሳኔ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ሲሆን ይህ ዓይነቱ እውቀትና ምክንያታዊነትን ያነገበ አካሄድ አሁን ላሉብን ዘርፈ ብዙ ችግሮቻችን መንገድ ከፋች እንደሚሆን ያሳያል።

እንዲህ ዓይነቱ በጥናት ላይ የተመሠረተ የውሳኔ ትግበራ በሰራዊት ረገድ ሉአላዊት አገር ከመፍጠር ጎን ለጎን የኢኮኖሚ አቅማችንን በማስተሳሰር የሰራዊታችንን የስልጠና፣ የትጥቅና የኑሮ ሁኔታ ከማሻሻል አኳያ ከፍተኛ ጥቅም አለው። ከዚህ ከፍ ሲልም የምንፈልጋትን ሉአላዊት አገር በተጠናከረ ሰራዊትና በታመነ አቋም ለመፍጠር መተማመኛ የሚሰጠን ነው።

«ሁሉንም የክልል ልዩ ኃይሎች እንደገና የማደራጀቱ ተግባር ለዘላቂ የአገር ጥቅም እና ደህንነት ነው» ሲል መንግሥት በመግለጫው አጽንኦት ሰጥቶ ያስታወቀ ሲሆን፣ ከዚህ እውነት በመነሳት ወደ'ማያሻማ ተግባቦት መሄድ ይቻላል።

ከዚህ የመንግሥት መግለጫ ጎን ለጎን የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ ሰላማዊት ካሳ መንግሥት በክልል ልዩ ኃይሎች ላይ ያወጣው የትግበራ እንቅስቃሴ የሁሉንም ክልል ልዩ ኃይል አባላት መልሶ የማደራጀት ሥራ እንጂ ከትጥቅ ማስፈታት ጋር የሚያያዝ እንዳይደለ ተናግረዋል።

እንቅስቃሴው አንዳንዶች እንደተረዱት ሳይሆን የአገር ሉአላዊነትን ከማስጠበቅ፣ አገር ውስጥ ሆነ ከውጭ የሚሰነዘርን ጥቃት ከመከላከል አንጻር ጠንካራ ሰራዊት ለመገንባት የሚያስችል እድል መፍጠር ነው ብለዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የክልል መንግሥታትም ተመሳሳይ አቋምን በማንጸባረቅ ላይ ይገኛሉ።

ቀደም ባለው ጊዜ እንዳየነው የክልል ልዩ ኃይል በክልሎች መካከል የደህንነት ዋስትና መሆኑ ቀርቶ መፎካከሪያ ነበር። አገር የምትባለውን ትልቅ እውነት በመተው ስለክልልና ስለታጠቁት መሣሪያ ሙግት ውስጥ ገብተው ታዝበናል። እንዲህ ዓይነቱ ያልተገባ አካሄድ አገራችንን በእኔነትና በራስ ወዳድነት ከማጎሳቆል ባለፈ አንድነት አይሰጠንም።

በመሠረቱ የክልል ልዩ ኃይልን የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እውቅና አይሰጠውም። በአንድ አገር ላይ በብሔር ስብጥር የቆመ አንድ መከላከያ ሰራዊት እንደሚያስፈልግ ሕገ መንግሥቱ ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ በኩል ብናልፍ እንኳን አሁን ላይ መንግሥት እያደረገ ያለውን፣ ልዩ ኃይልን የማዋቀር መግለጫ ልክ ሆኖ እናገኘዋለን።

ሕገመንግሥቱ እውቅና ያልሰጠው የጸጥታ መዋቅር አንዳንዴም ለአገር ስጋት መሆንን የሚጭር ነው። ሕገ መንግሥቱ እውቅና ባልሰጠው የክልል ልዩ ኃይል በኩል ክልሎች አዲስ አስተሳሰብን እየተለማመዱ የመጡበት ሁኔታ እየተስተዋለ ነው። በኢኮኖሚና በለውጥ መፎካከር ሲገባቸው ልዩ ኃይላቸውን ለመፎካከሪያነት የሚጠቀሙ ክልሎች እየተፈጠሩ ነው። ይህ እንግዲህ አገር ላይ አደጋ የሚደቅን ‹የእኔ እበልጥ እኔ› አጉል ልምምድ መሆኑ ነው።

በእርግጥ መልስ የሚፈልጉ ከሕዝብ የሚነሱ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። መንግሥት አገራችን በብዙ ችግር ውስጥ ባለችበት በዚህ ሰዓት እንዲህ ዓይነቱን ውሳኔ መወሰን ለምን መረጠ? የሚሉ ጥያቄዎች። አንዳንዶች ሕወሓት ትጥቁን ፈትቶ ባልጨረሰበት ሁኔታ የክልል ልዩ ኃይሎችን ለእንዲህ ዓይነቱ ትግበራ ማስገደድ አገራችንን ለዳግም ችግር መዳረግ ነው ብለው የሚሰጉ አሉ።

እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች በመንግሥት መግለጫ ላይ መልስ ተሰጥቶባቸዋል። በመጀመሪያ ደረጃ እየተሠራ ያለው ለየትኛውም አገራዊ ችግር አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥ የጦር ሰራዊት ለመገንባት ነው። ሕወሓትን በተመለከተ ለሚነሳው ጥያቄ ደግሞ በፕሪቶሪያው ስምምነት መሠረት የትጥቅ መፍታትን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት የስምምነት ሂደት እየተተገበረ እንደሆነ ተገልጿል።

ሕዝብ ከመንግሥት አሠራር ጋር በተያያዘ የሚያነሳቸው የስጋት ጥያቄዎች ልክ የሆኑና መበረታታት ያለባቸው ናቸው። ሆኖም ግን መረጃን መሠረት ያደረጉና ምክንያት ለበስ ቢሆኑ የበለጠ አዋጭ ይሆናሉ። አሁን ላይ የልዩ ኃይልን አደረጃጀት በተመለከተ ሁለት ዓይነት አረዳዶች እየተፈጠሩ ነው።

አንደኛው አረዳድ በመንግሥት በኩል የወጣው መግለጫና ብዙኃኑ የተረዳው ጠንካራ አገርና ጠንካራ ሰራዊት የመፍጠር አመኔታ ነው። ሌላኛው በአንዳንድ ክልሎች በተለይም በአማራ ክልል እየተስተዋለ ያለው የስጋትና የልዩ ኃይል ትጥቅ የመፍታት ፍራቻ ነው።

ምንም ሆነ ምን፣ እውነትን ማወቅ ነው አርነት የሚያወጣን። በተጣረሰ አካሄድና እውነትን በመሳት መንገድ ላይ የምንፈልገውን ለውጥ ማምጣት አንችልም። የሕዝብ ስጋት በመንግሥት የተደጋገመ እውነት ሊጠራ ይገባል። የሕዝብ ጥያቄ በመንግሥት ታማኝ መግለጫ ሊመለስ ግድ ይለዋል።

ስለአገራችን እውነታችንን የነጠቁን፤ እንዳይገባን አድርገው ያስቀመጡን ሰዎች አሉ። በለመዱት የጥላቻ እውቀት ስለጥላቻ ብቻ እንድናስብ ህሊናችንን የጋረዱብን ሰዎች። የገባቸውን ይደብቁንና ያልገባቸውን ይሰጡናል። እኛም ባልገባቸው ላይ ተንጠራርተን የገባቸውን አገር ወዳዶች እናውካለን። አሁን ላይ እየሆነ ያለው እንዲህ ነው።

የገባቸውን እውነት የሚያካፍሉን ሰዎች ያስፈልጉናል። በአንድነትና በፍቅር የቆሙ፣ ስለኢትዮጵያ ሁሉንም ዓይነት መስዋዕት ለመክፈል የተዘጋጁ ልቦች ያስፈልጉናል። ከቻሉ የገባቸውንና የሸሸጉትን እውነት አውጥተው ስለአገርና ሕዝብ «እውነቱ ይሄ ነው» ብለው ይንገሩን። ያለዛ በውሸት ትርክት ሳይገባን ነውጥ ፈጣሪ ባያደርጉን መልካም ነው።

መንግሥት በሰከነ መንገድ ሕዝቡን የማሳመን ሥራ ደግሞና ደጋግሞ መሥራት ይጠበቅበታል። ሕዝብም የመንግሥትን የሉአላዊነት መሻት በመረዳት ከጎኑ ሊሆን ይገባል። የመንግሥት ሀሳብ ሕዝብ ላይ ሲሠራ፣ የሕዝብ ሀሳብ መንግሥት ላይ ሲታይ ነው ለውጥ የሚመጣው።

የልዩ ኃይል እንደ አዲስ መደራጀት የአንድ ወቅት የሕዝብ ጥያቄ ነበር። መንግሕት ጊዜ ጠብቆ በሕዝብ ጥያቄም ሆነ በሕገመንግሥቱ መሠረት ትግበራ ጀመረ። አንዳንዶች ሲቀበሉት አንዳንዶች ስጋት ያዛቸው። በመንግሥት ሀሳብ ላይ ሕዝብ የትኛውንም ጥያቄ የማንሳት መብቱ የተጠበቀ ነው። ሆኖም ግን የአደረጃጀቱን አላማ በመረዳት ይሁንታን ማሳየቱ ለመንግሥት ጉልበት መሆን ጭምር ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ በእንዲህ ዓይነት መልኩ ካልተገነባችና በተጠናከረ ሰራዊት ካልተጠበቀች ህልውናችን አደጋ ላይ ነው የሚወድቀው። ከዚህም ከዚያም እንደምንሰማው ለውጥና እድገታችንን ተከትሎ ከተለያዩ አገራት ትንኮሳ እየደረሰብን ነው። ይሄን ዓይነቱ የሉአላዊነት ጥያቄ በአስተማማኝ መንገድ የሚመለሰው ደግሞ አስተማማኝ መከላከያ ሰራዊት ስንገነባ ነው።

የልዩ ኃይል አደረጃጀትም ኢትዮጵያን ከመጠበቅና የሕዝብ ደህንነትን ከማረጋገጥ አኳያ ብናየው የተሻለ ነው የሚሆነው። ከዚህ ውጪ የምንሰማቸው አሉባልታዎችም ሆኑ ከእውነት የራቁ መረጃዎች ያለምነውን ግብ እንዳንመታ እንቅፋት ከመሆን ባለፈ ምንም አይፈይዱልንም።

የተሳሳተ አረዳድ የተሳሳተ ድርጊትን ነው የሚፈጥረው። የተሳሳተ ድርጊት ደግሞ በአገርና ሕዝብ ላይ መከራ ነው የሚጥለው። እውነትን በመሻት አረዳዳችንን አስተካክለን የተሻለች አገር ብንፈጥር ትርፉ የጋራችን ነው። እውነትን አጣመውና አዛንፈው መንግሥትን ከሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ለማድረግ እንቅልፍ የማይተኙ አገር ጠል ኃይሎች ጥቂት አይደሉም።

አለማመናችን ለእነዚህ ኃይሎች መንገድ መክፈት ነው የሚሆነው። መንግሥት ሕዝብን ሊያምን፣ ሕዝብም መንግሥትን ሊያምን ይገባል። መተማመን በሌለው የመሪና የተመሪ ፖለቲካ ውስጥ ዛሬን ልክ ብንሆን ነገን ልክ መሆን አንችልም። ልዩ ኃይልን በተመለከተ የመንግሥት መግለጫ መንግሥት ለሕዝብ የሰጠው የእምነት ቃሉ ነው።

የመተማመን ፖለቲካ ነው ሩቅ የሚወስደን። መንግሥትና ሕዝብ ካልተማመኑ አገር ማለት ትርጉም ያጣል። ሕዝብ መንግሥትን በእምነት ሊቀበለው መንግሥትም በእውነት ሕዝብን ሊመራ ያስፈልጋል። የምናያቸውና የምንሰማቸው ነገሮች ናቸው ዛሬ ላይ መተማመናችንን ያጠፉብን።

የልዩ ኃይል አደረጃጀት ነገ ላይ ጠንካራዋን ኢትዮጵያ የምንፈጥርበት መንገድ እንደሆነ ከመንግሥት መግለጫ አረጋግጠናል። ይሄን እውነት በመቀበል ለትግበራው መንገድ መጥረግ ሕዝብ ኃላፊነቱን የሚወጣበት አንዱ ማሳያ ነው። አገራችን ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ አገራት የሉአላዊነት መደፈር ሲደርስባት ነበር።

ይህን መሰሉን ጥቃት ለመከላከል በመንግሥት በኩል ከተወሰዱ እርምጃዎች አንዱ መከላከያ ሰራዊትን ማጠንከር ነው። በዚህም መሠረት የክልል ልዩ ኃይሎች ከነሙሉ ትጥቃቸው ወደ ፈለጉት የጸጥታ መዋቅር እንዲገቡ እድል ተፈጥሮላቸዋል። እዚህ ጋ አጽንኦት የሚሰጠው አንድ ሀሳብ ቢኖር ትጥቅ መፍታትና ከነትጥቅ ወደ ፈለጉት የጸጥታ መዋቅር መግባት የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች እንደሆኑ ነው።

ብዥታችንን ማጥራት አለብን። መንግሥት «የክልል ልዩ ኃይሎች ትጥቃቸውን ይፈቱ» አላለም። አንዳንዶች ትጥቅ ፍቱ እንደተባለ አድርገው የሚያስቡ አሉ። ትጥቅ መፍታትና ከነሙሉ ትጥቅ ወደ ጸጥታ መዋቅር መግባት የተለያዩ ናቸው። ችግር እየፈጠሩብን ያሉ በቀጥታ ሳይሆን በተጓዳኝ የምንሰማቸው አሉባልታዎች ናቸው።

ወቅታዊውን አሉባልታ በተመለከተ በመንግሥት በኩል የተሰማው መግለጫ የልዩ ኃይልን አደረጃጀት፣ አላማና ትግበራ ያጠራ ነው። የትግበራ ሂደቱ የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት እንደሆነ መተማመን ላይ ተደርሷል። ይሄ መተማመን ከመንግሥት ወደ ሕዝብ የወረደ፣ ከሕዝብ መልሶ ወደ መንግሥት የተላለፈ አገር የመፍጠር የጥንካሬና የአይበገሬነት ማሳያ ነው።

ይህ ጥንካሬና አይበገሬነት ደግሞ የክልል ልዩ ኃይሎች የመንግሥትን ጥሪ ተከትለው ለአንድ አገርና ለአንድ ሕዝብ ይሁንታን ሲያሳዩ የሚጸና ነው። አንድን እውነት አስር ቦታ ከፍለን በፈለግነው መንገድ በመረዳት ማሸነፍ አንችልም። አሸናፊነታችን ያለው በሕዝብና መንግሥት መተማመን ውስጥ ነው። እንደአገር መቀጠል የምንችለው በጋራ ሀሳብ ለጋራ ትልም ስንደክም ነው።

ከብዥታ ወጥተን ወደ'ሚጠቅመን እውነት ማማተር ነው አገር የሚሰጠን። ጥያቄዎቻችን የአገር ጠላቶች የፈጠሯቸው እንዳይሆኑ ራሳችንን እንፈትሽ። ለአገራችን የሚበጃት የቱ እንደሆነ በመንግሥት በኩል የተነገረን የአደረጃጀት ትግበራ አለ። በዚያ እውነት ውስጥ መክረንና ዘክረን ጠንካራዋን ኢትዮጵያ ከመፍጠር ሌላ አስተማማኝ አማራጭ የለንም።

መንግሥት በሰከነ መንገድ ሕዝቡን የማሳመን ሥራ ደግሞና ደጋግሞ መሥራት ይጠበቅበታል። ሕዝብም የመንግሥትን የሉአላዊነት መሻት በመረዳት ከጎኑ ሊሆን ይገባል። የመንግሥት ሀሳብ ሕዝብ ላይ ሲሠራ፣ የሕዝብ ሀሳብ መንግሥት ላይ ሲታይ ነው ለውጥ የሚመጣው

# ወቅታዊ

# ‹‹የፊና ኦሮሚያን ፕሮጀክት አዋጭነት ስናስተውል እስካሁን ባለመጀመራችን በእጅጉ አስቆጭቶናል››

*-ኢንጂነር ዓለሙ ረጋሳ*
*የኦሮሚያ መስኖና አርብቶ አደር ምክትል ቢሮ ኃላፊ*


ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አስቴር ኤልያስ

ውሃ የለም ማለት ሕይወት የለም እንደማለት ነው። ውሃ ሲያጥር ደግሞ ድርቅ ጉልበት ያገኛል። በአንድ አካባቢ ለተከታታይ ዓመታት ዝናብ አልዘነበም ማለት ድርቅ ይበረታል ማለት ነው። በቦረና ዞን በግልጽ የታየውም ይኸው ችግር ነው። በዞኑ እስካለፈው መጋቢት ወር ድረስ ውሃ የተጠማው አርብቶ አደሩ ብቻ አይደለም፤ ወይም ደግሞ እርሱ የሚያረባቸው እንስሳቱ ብቻ አይደሉም፤ ሳር ቅጠሉ ጭምር እንጂ።

መሬቱ ከውሃ ጥም የተነሳ ገጹ ላይ የሚታይ አረንጓዴ ነገር አልነበረውም። ይህ ግን በጥቂት ቀናት ዝናብ ተሸሯል፤ ምንም እንኳ በአካባቢው ወንዝ የሚባል ባይኖርም መጋቢት ላይ በዞኑ በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ዝናብ መጣሉ ሕይወት ላለው ሁሉ እፎይታን ሰጥቷል፤ የተጠማ ረክቷል። ይህ ዝናብ ወቅታዊ እንደመሆኑ እርካታው ዘላቂ መሆን አይችልም፤ በመሆኑም ዘለቄታ ያለው እንዲሆን ለማድረግ የኦሮሚያ ክልል አስቀድሞ በ2014 በጀት ዓመት በጀመረው ‹‹ፊና ኦሮሚያ›› ፕሮጀክት በተለያዩ የክልሉ ዞኖች ግድቦችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። ክልሉ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እነዚህን ግድቦች ለመገንባት የተነሳው በዋናነት ቦረና አካባቢ የተከሰተው አይነት ድርቅ ለመከላከል ነው። የ ‹‹ፊና ኦሮሚያ›› ግድብ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ በመጀመሪያ ውሃ መያዝ ሲሆን፣ ይህም የውሃ ጥምን የሚያረካ፣ ምግብ የሚሆን፣ የአየር ንብረትን ጭምር የሚያስተካክል ብሎም የስራ እድልንም እየፈጠረ ያለ ትልቅ ፕሮጀክት ነው።

ይህንኑ የፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክቶችን ግንባታ በምክትል ደረጃ በመምራት ላይ ካሉ የኦሮሚያ ክልል መስኖና አርብቶ አደር ምክትል ቢሮ ኃላፊ ከሆኑት ከኢንጂነር ዓለሙ ረጋሳ ጋር ስለፕሮጀክቱ አጠቃላይ አተገባበርና ጠቀሜታ አዲስ ዘመን ቆይታ አድርጎ እንደሚከተለው አጠናክሯል።

**አዲስ ዘመን፡-የ‹‹ፊና ኦሮሚያ›› ፕሮጀክት ዋና ዓላማ ምንድን ነው? ተግባራዊ የሚሆነው በየትኞቹ የክልሉ አካባቢዎች ነው?**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** ፊና ከሚለው ስያሜ ብጀምር ደስ ይለኛል፤ ፊና ማለት በአፋን ኦሮሞ ልጅ እንደማለት ነው፤ በአሁኑ ወቅት ውሃ ከልጅ እኩል ይቆጠር ጀምሯል። በተለይ በቦረና አካባቢ ደግሞ እንደሚታወቀው በቅርቡ የተከሰተው ድርቅ ከውሃ ማጣት የተነሳ በመሆኑ በዞኑ ማኅብረሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። ከዚህ የተነሳ በቦረናዎች ዘንድ ውሃ ትርጉሙ ከፍ ያለ በመሆኑ ከልጅ እኩል የሚታይ የተፈጥሮ ስጦታ ነው።

በፊና ኦሮሚያ እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች ሲያጋጥመን ለነበረው ድርቅ እንደ ሁነኛ መፍትሔ የሚቆጠር ነው። የፕሮጀክቱ ዓላማ በዋናነት ውሃ መያዝ ሲሆን፣ በመቀጠል ደግሞ ከሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የመስኖ ስራ እና እንደ ዓሳ ምርትና ሌሎች ተግባራት የሚከናወኑበት ይሆናል ማለት ነው።

በኦሮሚያ በድርቅ የሚጠቁ ወደ ስምንት ዞኖች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ሁለቱ ቦረናዎችና ሁለቱ ባሌዎች እንዲሁም ሁለቱ ሐረርጌዎችና ጉጂ ተጠቃሽ ሲሆኑ፤ አብዛኛው በሚያስብል ደረጃ 60 በመቶ ያህል ፕሮጀክቶቹ ያሉት በእነዚህ ዞኖች ላይ ነው። በጥቅሉ ሲታይ ግን ፕሮጀክቱ በሁሉም

**በፊና ኦሮሚያ እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች ሲያጋጥመን ለነበረው ድርቅ እንደ ሁነኛ መፍትሔ የሚቆጠር ነው። የፕሮጀክቱ ዓላማ በዋናነት ውሃ መያዝ ሲሆን፣ በመቀጠል ደግሞ ከሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የመስኖ ስራ እና እንደ ዓሳ ምርትና ሌሎች ተግባራት የሚከናወኑበት ይሆናል ማለት ነው**

የኦሮሚያ አካባቢ የሚገኝ ነው። ለአብነትም ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ወለጋ እና ሌሎችም ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክት አለ ማለት ይቻላል።

ሌሎችም የውሃ አሊያም የዝናብ ችግር የለባቸውም የተባሉ ዞኖች ላይ የተለያዩ የውሃ እጥረት ያለባቸው ወረዳዎች አሉ። እነዚህን ቦታዎች በመለየት በተለይ በጎርፍ የሚባክነውን የዝናብ ውሃ በመያዝ ለሕዝቡ ልማት ለማዋልና በክልላችን ላይ ያለውን የውሃ እጥረት ለመቅረፍ እንደ ኦሮሚያ ክልል እቅድ ይዘን በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን።

በ2014 ዓ.ም ላይ የጀመርነው ወደ 73 ፕሮጀክቶችን ነው። ከእነዚህ ውስጥ ቦረና ላይ እየገነባን ያለነው ወደ 14 ግድቦችን ነው። በቦረና አካባቢ ትልቁ እጥረት ውሃ ነው። ከዚህ የተነሳ በቦረና ውሃ ይዞ ማቆየት ታላቅ ተግባር ነው። ፊና ኦሮሚያም ያደረገው ይህንኑ ነው። በቦረና በተጀመረው ግድብ ለአርብቶ አደሩ ውሃ ሲያዝለት ለተለያዩ ተግባራት ሊያውለው ይችላል። በተለይ ለመጠጥ ውሃነት እንዲሁም ለመስኖ ልማት ሊጠቀምበት ይችላል። ትልቁ ሀብት ለሆነው እንስሳው ደግሞ መኖ ሊያለማበት ይችላል። ስለዚህ የፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክቶች እንደክልል ሲታሰብ የሕዝብን የአኗኗር ዘዴ መለወጥ የሚችል ነው ማለት ይቻላል።

እንደ ኦሮሚያ ክልል ውሃ ለመያዝ ያለው እምቅ አቅም በጣም ትልቅ ነው። በመሆኑም ወደ 73 ግድብ መስራት መጀመራችን ውሃ እንይዛለን በሚል እምነት ነው። ከዚህ ከ73ቱ ግድቦች ደግሞ 14ቱ አስቀድሜ እንደጠቀስኩት በቦረና እየተሰሩ ያሉ ናቸው። ከእነዚህ 14ቱ ውስጥ ከሶስቱ በስተቀር ሁሉም ወደማጠናቀቂያው የተቃረቡ ግድቦች ናቸው። ወደ ዘጠኝ ያህሉ ግድቦች ደግሞ እየተጠናቀቀ በመሆኑ እያንዳንዳቸው ውሃ በመያዝ ላይ ይገኛሉ።

በዞኑ ከሚገኙ ከአንዱ ግድብ ማለትም በአሬሮ ወረዳ ፉልዱዋ ቀበሌ ከሚገኘው ከፉናን በሬሳ ግድብ ፕሮጅክት ብቻ ከ17 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ በላይ መያዝ የሚቻል ነው። አሁን ባለው ሁኔታ በዚሁ በአንዱ ግድብ በሁለትና በሶስት ቀን ዝናብ ብቻ ወደ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ መያዝ ተችሏል። ይህ ቁጥር ምናልባትም ዝናብ ሲዘንብ ከፍ የሚል እንደሆነም ይታወቃል። ይህ የያዘው ውሃ ብቻ እንኳ ቢሆን ለሕዝቡ ለዓመት ያህል የሚበቃው ይሆናል።

አሁን እየተሰማን ያለው ነገር እነዚህ ግድቦች ምነው ቀደም ብለን በጀመርናቸው የሚል ቁጭት ነው።ሕዝባችንን ማዳን ስንችል እነዚህ ፕሮጀክቶች ቀደም ብለው ባለመሰራታቸው ምክንያት ብቻ ሕዝቡ ትልቅ ችግር ውስጥ ወድቆ ቆይቷል።ክልሉ በቦረና ብቻ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ወደ 2 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በጀት በጅቶ ነው።

በአጠቃላይ ከፊና ውጪ ወደ 28 ፕሮጀክቶች ደግሞ አሉ፤ እነዚህም የመጠጥ ውሃ፣ አነስተኛ መስኖዎች እንዲሁም ከወንዝ የሚጠለፉ ፕሮጀክቶች ናቸው። ከዚህ የተነሳ እነዚህን መሰል ፕሮጀክቶች መስራት ማለት የሕዝቡን የአኗኗር ዘይቤ ወደተሻለ ደረጃ መቀየር ማለት ነው። ፊና ኦሮሚያ ደግሞ ከእነዚህ ውስጥ ተጠቃሽ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የፊና ኦሮሚያ የግድብ ስራ ወደስራ የገባው በምን ያህል በጀት ነው?**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** የፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክት ተለይቶ የተሰራው የውሃ እጥረት አለባቸው በተባሉ አካባቢዎች ነው። አጠቃላይ እንደ ኦሮሚያ ከ22 ቢሊዮን ብር በላይ ተበጅቶ በመሰራት ላይ ይገኛል። በዚሁ ውስጥ በመስኖ ሚኒስቴር የሚደገፉ አሉ። ይህ 22 ቢሊዮን ብር የመጀመሪያ ስምምነት በተፈረመበት ጊዜ የተቀመጠ ነው። ከዚያ በኋላ ወደተግባር ሲገባ እያንዳንዱ ፕሮጀክት የራሱ የሆነ በትንሹ ከ15 እና 20 በመቶ ልዩነት በማምጣቱና የጥናትም ለውጡ በመደረጉ ሲደማመር እስከ 30 ቢሊዮን ብር ይደርሳል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ክልልም ሆነ እንደ ቦረና ዞን እየተገነቡ ያሉ ግድቦች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ይችላሉ?**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** እንደሚታወቀው በቦረና ለተከታታይ አምስት ዓመታት ዝናብ አለመዝነቡ የሚታወቅ ነው። አምና በአንዳንድ ቦታዎች በዘነበው ዝናብ ዓመቱን ሙሉ ሕዝቡ መጠቀም ችሏል። ከአስር ሺ በላይ የሚሆኑ ግመሎችና ፍየሎች ከዝናብ ውሃ ሲጠቀሙ ቆይተዋል። አሁን ደግሞ የተያዘው ውሃ ትልቅ ስለሆነ በርካቶች ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ። በመጀመሪያ ዋናውና ትልቁ ጉዳይ የውሃው መያዝ ነው። ውሃው በተፈለገ ልክ መያዝ ማለት ፋይዳው ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ከመጠጥነት ባለፈ ተጨማሪ በርካታ አገልግሎት እንደሚሰጥ ታስቦ እየተሰራበት ይገኛል።

በቦረና ውስጥ ያሉ ግድቦች በሙሉ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ይጠናቀቃሉ። ከእነዚህ ውስጥ አስቀድሞ መቶ በመቶም የተጠናቀቀ ግድብ አለ። አብዛኞቹ ግድቦች የሚሰሩት በአፈር በመሆኑ እምብዛም የሲሚንቶ ግብዓት አያስፈልጋቸውም። ኢንቴክ አካባቢና ውሃው በጣም ሲሞላ ማስተንፈሻ የምንለው ስራ የሚሰራው በሲሚንቶ ነው። ይህ በመሆኑም ብዙዎቹ ግድቦች የቀራቸው የሲሚንቶ ግብዓት የሚያስፈጋቸው ላይ ነው። ያም ቢሆን እስከ ሰኔ 30 ይጠናቀቃሉ።

በአጠቃላይ ከ73ቱ መካከል 30 ግድቦች በዘንድሮ ዓመት የሚጠናቀቁ ሲሆን፣ በተለይ በሁለቱም ባሌዎችና በሁለቱም ሐረርጌዎች

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

እየተገነቡ ያሉት ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃሉ ተብሎ እየተሰራ ነው። ግድቦቹ ይጠናቀቃሉ ብለን ስንል በመደበኛ ሰዓት ብቻ በመስራት ሳይሆን ከመደበኛ የስራ ሰዓት ተጨማሪ ሰዓት ተወስዶ ነው። እንዲህም ሲባል ፈጥኖ ለማጠናቀቅ ይረዳ ዘንድ እየተሰራ ያለው ለ16 ተከታታይ ሰዓት ሲሆን፣ ይህም ተግባራዊ እየተደረገ ያለውም በሁለት ፈረቃ ነው። እነዚህ ግድቦች የተጀመሩት ባለፈው ዓመት ሲሆን፣ በኦሮሚያ ላይ በጣም ትልቅ ልምድ ያገኘንበት ነው።

እንደሚታወቀው ከዚህ ቀደም ምንም እንኳ ይዞታቸው ከፍ ያለ ቢሆንም እነዚህን መሰል ግድቦች በሀገር ደረጃ ለመገንባት ታስቦ ወደስራ ከተገባ በኋላ የሚያሳዩን ልምድ አስርና አስራ አምስት ዓመት መፍጀታቸውን ነው። አሁን ግን እየተከተልን ያለው እንደ እሱ አይነት አካሄድ ሳይሆን መጠናቀቅ ያለበት በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው በሚል በጣም በቁርጠኝነት ነው። ከዚህም የተነሳ ባጠረ ጊዜ የያዝናቸውን የግድብ ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ በትልቅ ተነሳሽነት እየሰራን ነው።

ግድቦቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ደግሞ መንገዶችም ጎን ለጎን በመሰራት ላይ በመሆኑ የግድቡ መጀመር ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው ማለት ይቻላል። በአጠቃላይ በእስካሁኑ ስራቸው ተጀምሮ በመጠናቀቅ ላይ ባሉ በ73ቱ ግድቦች አካባቢ ወደ 210 ኪሎ ሜትር መንገድ ተሰርቷል። በዚህ ስራ ላይ ስራ አጥነትን ከመቀነስ አኳያም ጎን ለጎን ስራዎች እየተሰሩ ነው ። በአንድ የግድብ ፕሮጀክት ብቻ እንኳ ካስተዋልን አምስት አማካሪ መሐንዲሶች ይቀጠራሉ። ከእነዚህ ውጪ ሰርቬየሮችና ፎርማኖች ደግሞ አሉ። በአጠቃላይ በፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክት የሚገነቡ ግድቦች ላይ ከ14 ሺ ሰው በላይ ተቀጥሮ እየሰራ ይገኛል። በቋሚነት፣ በጊዜያዊነትና በቀን ሰራተኝነት ሰራተኞችን ማሳተፍ የቻለ ፕሮጀክት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አስቀድመው እርስዎ እንደጠቀሱት ከዚህ በፊት እንደሀገር ያለው የስራ አፈጻጸም የሚያረካ አይደለም፤ ከፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክት ሊወሰድ የሚችለው ልምድ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ የፊና ኦሮሚያን ፕሮጀክት አዋጭነት ስናስተውል እስካሁን ባለመጀመራችን በእጅጉ አስቆጭቶናል ማለት እወዳለሁ። ምክንያቱም ደግሞ እነዚህ ግድቦች ባለመኖራቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ እንስሳት አልቀዋል። ከዚህ የተነሳ በተለይ ቦረና ላይ አርብቶ አደሩ ባዶ እጁን ቀርቷል። እየኖረ ያለውም ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር በሚደረግለት ድጋፍ ነው። ይህ ስራ አስቀድሞ ተሰርቶ ቢሆን እርዳታ መቀበል አይደለም መልሶ መርዳት የሚችል ሕዝብ ነው። ለዚህ ደግሞ ምንም ጥርጥር የለውም። ሰፊ መሬት አለ፤ መሬቱ መስፋቱ ብቻ ሳይሆን ለእርሻ የሚመችም መሆኑ ትልቅ ነገር ነው። ለሰብል፣ ለፍራፍሬም ሆነ ለአትክልት መሆን የሚችል ለም መሬት ነው። በቦረና ያለው መሬት ለምሳሌ ስንዴም ጤፍም ማምረት የሚያስችል ነው። ይህ ሁሉ አቅም እያለን ካለመስራታችን የተነሳ ሕዝቡ ለድርቅ ተጋልጦብናልና ይህ የሚያስቆጨን ጉዳይ ሆኖብናል ማለት እችላለሁ።

እንደምታስታውሺው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አንድ መቶ ግድቦችን እንገነባለን ብለው ነበር፤ እኛም ተነሳሽነቱን የወሰድነው ከዚህ ነው። መቶ ግድብ የተባለው እንደ ሀገር ነው ፣ እኛ ደግሞ እንደ ክልል ወደ 73 ግድቦችን ጀምረናል። ይህን ስራ ሁሉም ክልል እንዲሰራው መበረታታት አለበት ባይ ነኝ። ለምሳሌ ሶማሌ፣ ደቡብና ሌላም ክልል ድርቅ አለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ድርቅን ሊያጠፋ የሚችል አቅም እንደ መሬትና ውሃ ደግሞ በየክልሉ አለ። በተለይ በስፋት ዝናብ የሚዘንብባቸው አካባቢዎች አሉን። በተቃራኒው ደግሞ ልክ እንደ ቦረና ሁሉ ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች አሉ። ስለዚህ ይህ በኦሮሚያ ክልል የተጀመረው አይነት የግድብ ስራ በሌሎችም ክልሎች ሊበረታታና ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። ይህን ሀገራችንን ወደተሻለ ደረጃ ከፍ የምናደርግበት አንዱ መፍትሔ ነው እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በፊና ኦሮሚያ እየተገነቡ ያሉ ግድቦች ሕዝቡ የሚጠቀምባቸው በምን አግባብ ነው? ከውሃው ማቅረብ ባሻገር በቀጣይ ምንስ ድጋፍ ይደረግለታል።**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** አንደኛ ይህ የተያዘው ውሃ ለምሳሌ የቦረናን ወስደን ከሆነ ቦረና ዝናብ ሊያገኝ የሚችለው በዓመት ሁለቴ ነው። በመጋቢት አካባቢ ይዘንባል፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ የሚዘንበው እንደሌላው ብዙው የሀገሪቱ ክፍል ሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ ሳይሆን መስከረም ወር ላይ ነው። ከእነዚህ ጊዜያት በኋላ የሚታይ ምንም አይነት ዝናብ አይኖርም።

ስለዚህ እንደከዚህ ቀደሙ ወንዝ ላይ ብቻ እንደምንሰራው ስራ ማየት የለብንም። በአሁኑ ወቅት መስኖን ስናስብ ማልማት ያለብን ደጋ አካባቢ እንደምናየው አይነት ውሃ በስፋት ለቅቀን አይደለም። እኛ እንደኦሮሚያ ቢሮ እያሰብን ያለነው አንደኛ ቴክኖሎጂን መጠቀም ነው። የጠብታ መስኖን መጠቀም መቻል አለብን። ይህ ማለት ውሃ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅመን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማልማት አለብን ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ ቢሯችን እየሰራበት ይገኛል።

ሕዝቡ ደግሞ ውጤታማ በሆነ መንገድ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፤ ለምሳሌ እኛ እንደ ኦሮሚያ አንድ ሚሊዮን ሔክታር መሬት ላይ ስንዴ አልምተናል። አብዛኛው አንድ ሚሊዮን ሔክታር ላይ የለማው ስንዴ ግን መልማት የቻለው በፓምፕ አቅርቦት ነው። እንዲሁም ወንዞችን በቀላሉ በመጥለፍ ጭምር ነው። ይህንን በይበልጥ ማጎልበት የግድ ይለናል። ስትራክቸር መጠበቅ የለብንም። ለምሳሌ በቦረና እንዳልኩሽ ወደ ዘጠኙ ግድቦች ወደመጠናቀቅ ተቃርበዋል፤ አንዱ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፤ ቀሪዎቹ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ይጠናቀቃሉ።


ስለዚህ አሁን ፓምፖችን ለሕዝቡ እናቀርባለን፤ በግድቡ ዙሪያ ያሉ ቦታዎችም ለእርሻ ምቹ ይሆናሉ። አርብቶ አደሩ ደግሞ መንቀሳቀስ መቻል አለበት፤ በግድቡ የተያዘው ውሃ በቦይ እደጁ ድረስ እሲኪመጣም መጠበቅ አይኖርበትም። ፓምፕ ስለሚቀርብለት ከተያዘው ውሃ በፓምፕ መጀመር ይችላል። ገና ለገና ስትራክቸር አልተሰራለትም፤ የመስኖ ቦይ አልተገነባለትም ብለን አንጠብቅም። ትልቁ ዓላማችን ውሃን መያዝ ብቻ ነው። ከያዝን በኋላ ግን ቴክኖሎጂ ተጠቅመን ወዲያውኑ ወደ ልማት እንገባለን እንጂ የምንጠብቀው ሌላ ነገር አይኖርም።

ሌላው የመጠጥ ውሃ ሲሆን፣ ለምሳሌ ቦረና ምንም አይነት የመጠጥ ውሃ የለም። አንድ ጀሪካን እስከ 60 ብር ድረስ ይሸጣል። ከዚህም የተነሳ የመጠጥ ውሃ ለሕዝቡ እየተከፋፈለ ያለው በቦቴ ነው። የክልሉ መንግስት ቦረና ዞን ላይ ብቻ ወደ መቶ የሚጠኑ ቦቴዎችን በኪራይ አስገብቶ ውሃ እንደሬሽን እያከፋፈለ ነው። ስለዚህ ውሃ በተገነቡ ግድቦች መያዝ ለዚህም እጥረት ትልቅ መፍትሔ ነው።

በተጓዳኝ ደግሞ ከተለያዩ ሴክተሮች ጋር እንደ ግብርና ሚኒስቴር፣ የደንና ዱር እንስሳት ጥበቃ እንዲሁም የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት የምንሰራቸው ስራዎች አሉ። ከዚህ ጎን ለጎን በግድቡ ዓሳ ማርባት ይቻላል። የከብቶችን መኖ ማልማት ይቻላል። እንዲሁም ለቱሪዝምም የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። በተለይ ድርቅን በዘላቂነት ለመቋቋም በመጀመሪያ ደረጃ በገጸ ምድር ያለውን ውሃ መያዝ ወሳኝ እንደመሆኑ የፕሮጀክቱ መሰራት በገጸ ምድር የሚያዘው ውሃ በከርሰ ምድር ያለውን አቅም ከፍ የሚያደርገውም ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በቦረና ውሃ አጠር አካባቢዎች እየተገነቡ የሚገኙ ግድቦች የሚይዙት የውሃ መጠን ምን ያህል ነው ተብሎ ይታሰባል? ምን ያህሉስ አባወራ ተጠቃሚ ይሆናል?**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** በቦረና ዞን ብቻ ወደ 14 ግድብ እየተገነባ ሲሆን፣ ወጪውም ከሁለት ነጥብ



**ወደ ውሃ መጠኑ ሲመጣ በቦረና በተገነቡ ግድቦች ብቻ ከ50 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ በላይ መያዝ ይቻላል**

ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ነው። እንደ ኦሮሚያ ክልል እየተገነቡ ያሉ ደግሞ እንዳልኩሽ 73 ሲሆኑ፣ የተዋዋልንባቸው ገንዘብ ከ22 ቢሊዮን ብር በላይ ነው። የተጀመሩት 73ቱ ግድቦች ሲጠናቀቁ ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚጠይቁ ይሆናሉ ብለን እንጠብቃለን።

ወደ ውሃ መጠኑ ሲመጣ በቦረና በተገነቡ ግድቦች ብቻ ከ50 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ በላይ መያዝ ይቻላል። ለምሳሌ ከ14ቱ ግድቦች አንዱ አሬሮ ወረዳ፣ ፉልዶዋ ቀበሌ የሚገኘው የፊና ኦሮሚያ ፉናን በሬሳ ግድብ ፕሮጀክት ነው፤ ይህ ግድብ 17 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ እንደሚይዝ ይጠበቃል። ይህ ግድብ በጥቂት ቀን ውስጥ ብቻ በጣለው ዝናብ 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ መያዝ ችሏል። በጥቅሉ በቦረና ብቻ በሚያዘው ከ50 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ በላይ ውሃ ከመቶ ሺ በላይ የሚሆኑ አርብቶ አደሮች ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- አጠቃላይ በኦሮሚያ እየተገነቡ ካሉ 73ቱ ግድቦች ምን ያል ውሃ ይያዛል? በቀጣይስ የፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክት መርሃ ግብር የሚሆነው ምንድን ነው?**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** እኛ በፕሮግራማችን መሰረት የያዝነው እቅድ በአራት ዓመት ውስጥ ወደ 255 ፕሮጀክቶችን በኦሮሚያ ክልል መገንባት ነው። እንደሚታወቀው ከእነዚህ ውስጥ በ2014 ዓ.ም ወደ ግንባታ የገቡ ግድቦች የጠከስኳቸው ናቸው። ከ73ቱ ግድቦች ውስጥ 14ቱ በቦረና እንደሚገኙ ሁሉ በባሌ ደግሞ ስምንት አሉ። እነዚህ 73ቱ ግድቦች ሲጠናቀቁ ከ700 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ ውሃ ይይዛሉ ተብሎ ይጠበቃል። ከ50 ሺ በላይ ሔክታር መሬት እንደሚያለማም ይታሰባል።

እነዚህ ፕሮጀክቶች እንዳልኩት ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ የሚጠይቁ ቢሆንም በአብዛኛው ግን እየተገነቡ ያሉት ከአካባቢው በሚገኘው ጥሬ ሀብት ነው። በተለይ በቦረና ያሉት ግድቦች በኢንዱስትሪ ተፈብርከው ከሚወጡ እቃዎች ውጪ በአብዛኛው በአካባቢው ባለው ድንጋይና መሰል ግብዓት የሚገነቡ ናቸው። እነዚህ ከአካባቢው የሚገኙ ግብዓቶች ደግሞ ያለምንም ወጪ በነጻ የተገኙ ናቸው። ሕዝቡም በየአካባቢው እየተገነቡና ውሃ እየያዙ የሚገኙትን ግድቦች የውሃውን ጥቅም ከምንም በላይ ይረዳልና እንደገዛ ልጁ እያያቸው ይገኛል።

በቀጣይ ከ73ቱ በተጨማሪ ወደ 70 ግድቦችን ለመገንባት እቅድ ተይዟል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ጥናት እየተጠና ይገኛል። ድርቅ እያጠቃቸው ያሉ የኦሮሚያ አካባቢዎችን መፍትሔ እንዲያገኙ ለማድረግ በመጀመሪያ በዋናነት ውሃ መያዝ የግድ ነው። በተለይ ደግሞ ያለምንም ፋይዳ በሚዘንበው ከፍተኛ ዝናብ ሳቢያ በከንቱ የሚፈሰውን ውሃ በአንድ ላይ በመያዝ የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል በእቅድ ይዘናል።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በክልሉ እየተካሔደ ያለው የልማት እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** በኦሮሚያ ክልል በርካታ የተፈጥሮ ሀብት አለ። ለአብነት በገጸ ምድር ያለው ውሃ ማለትም ወንዞችን ጨምሮ ውሃ በመያዝ ብቻ ከአራት ሚሊዮን ሔክታር መሬት በላይ ማልማት የሚያስችል ነው። በከርሰ ምድር ባለው የውሃ ሀብት ደግሞ ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሔክታር በላይ የሚያለማ ሀብት አለን ማለት ይቻላል። ከዚህ አንጻር ሲታይ ምንም አልተሰራም ማለት ያስደፍራል። ከክልሉ ስፋትና ካለው አቅም አንጻር ሲለካ እስካሁን የተሰራ ስራ ብዙም የሚታይ አይደለም። ለዚህም ነው አንዳንድ አካባቢ በድርቅ ሲጠቃ የነበረው። ከዚህ በኋላ ግን በቁርጠኝነት ለመስራት የወሰንነው ይህን የድርቅ ችግር ለመግታት በማሰብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ኢንጂነር ዓለሙ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የኢንቨስትመንት አቅምን የማስተዋወቅ ዓለም አቀፍ ጥረት

አንተነህ ቸሬ

የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ዘርፍ በየጊዜው ከፍተኛ መሻሻልና እድገት ካስመዘገቡ ዘርፎች መካከል አንዱ ነው። አገሪቱ ያላት እምቅ የተፈጥሮ ሀብት እና ሰፊ የገበያ እድል፣ ያስመዘገበቻቸው ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገቶች፣ በተለይ በመሠረተ ልማት ዝርጋታ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባሮች እንዲሁም የኢንቨስትመንት ዘርፉ ማበረታቻዎች፣ አገሪቱን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መዳረሻ በማድረግ በአፍሪካ ደረጃ ቀዳሚ ከሚባሉ አገራት መካከል አንዷ እንድትሆን ማስቻላቸው ሲጠቀስ ቆይቷል። ይህ ሁሉ ለኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ማደግ ዓይነተኛ ሚና የተጫወተ ሲሆን፣ ለአገሪቱ ምጣኔ ሀብት እድገትም ትልቅ ድርሻ አበርክቷል።

ይሁን እንጂ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄደውን ጦርነት ተከትሎ በአገሪቱ ላይ የተደረጉ ጫናዎች፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታዩ የምጣኔ ሀብት ቀውስና ጦርነቶች ጋር ተዳምረው በአገሪቱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል። በተለይም ባለፈው ዓመት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከተካሄደው ጦርነት ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ክስተቶች በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደራቸው በተደጋጋሚ ተጠቅሷል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም ባለፈው ዓመት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትንና የተገኙ ውጤቶችን አስመልክቶ ይፋ ባደረገው መረጃ፣ ጦርነቱን ተከትሎ በኢትዮጵያ ላይ ጫናዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የኢትዮጵያ ከአጎዋ (AGOA) መታገድ እና የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ጫና በበጀት ዓመቱ ካጋጠሙ የኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ተግዳሮቶች መካከል እንደሚጠቀሱ ገልፆ ነበር።

ከጦርነት በኋላ በሚኖር የኢንቨስትመንት አስተዳደርና አመራር ብቻም ሳይሆን በሰላም ጊዜም ቢሆን የኢንቨስትመንት አቅሞችንና አማራጮችን በማስተዋወቅ ባለሀብቶችን መሳብና ዘርፉን ማሳደግ ይገባል። ይህን ለማድረግ ደግሞ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ባለድርሻ አካላትን የሚያገናኙ፣ የኢንቨስትመንት አቅሞችንና አማራጮችን የሚያስተዋውቁ መድረኮች ከፍተኛ ሚና አላቸው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት አቅም ለባለሀብቶች ማስተዋወቅን ዓላማቸው ያደረጉ ልዩ ልዩ መድረኮች እንደተካሄዱ ይታወሳል። በመድረኮቹ ቀላል የማይባሉ ውጤቶችም ተገኝተዋል።

የኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት አማራጮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ በሕግ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የአገሪቱን የኢንቨስትመንት አቅሞችና በዘርፉ ያሉ መልካም እድሎችን ለማስተዋወቅ ያለመ፣ ‹‹ኢንቨስት ኢትዮጵያ›› (Invest Ethiopia) የተሰኘ የኢንቨስትመንት ፎረም ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ይገኛል። ፎረሙ ከሚያዝያ 18 እስከ 20 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ፣ ስካይላይት ሆቴል እንዲካሄድ ቀጠሮ ተይዞለታል፤ ከ600 በላይ የኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ተዋንያን እንደሚሳተፉበት ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ተመስገን ጥላሁን እንደሚሉት፣ እንደ አገር ከኢንቨስትመንት ዘርፍ ዘላቂ የሆነና የተሻለ ጥቅም ለማግኘት በራስ ተነሳሽነት የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ሥራዎችን መሥራት ተገቢ በመሆኑ፣ ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት አቅም ማስተዋወቂያ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ይህን አሠራር ባለፉት ዓመታት በሚፈለገው ደረጃ መተግበር አልተቻለም። ባለፉት ሦስት ዓመታት የኮቪድ ወረርሽኝ የዓለም የኢኮኖሚ ሥርዓትን ሲያናጋ ቆይቷል። ከዚህ በተጨማሪም፣ በአገሪቱ የነበረው አለመረጋጋት በኢንቨስትመንት ፍሰቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ወደ መረጋጋት ተሸጋግራለች ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ የኮቪድ ወረርሽኝ ዓለም አቀፍ ስጋትነቱ መቀነሱንና በዓለም አቀፍ ደረጃ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል። አገራትም ያሏቸውን አማራጮች በማስተዋወቅ የኢንቨስትመንት ፍሰታቸውን ለመጨመር እየሠሩ መሆናቸውን ነው ያመለከቱት። ይህን ታሳቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከሌሎች አጋር የመንግሥት አካላት ጋር፣ በተለይም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በውጭ ከሚገኙ የዲፕሎማቲክ ሚሽኖች ጋር፣ በመተባበር ከሚያዝያ 18 እስከ ሚያዝያ 20 ቀን 2015 ዓ.ም የሚካሄድ ትልቅ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም እንዳዘጋጀ ገልፀዋል።

ምክትል ኮሚሽነሩ እንደሚሉት፣ የፎረሙ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ ያሏትን ዘርፈ ብዙ የኢንቨስትመንት አማራጮች ማስተዋወቅ ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኮቪድ ወረርሽኝ እና በግጭቶች ምክንያት ያልተዋወቁ አዳዲስ ለውጦች አሉ። ከአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችና መወዳደሪያ መስፈርቶች አሉ። ከእነዚህም መካከል ወደ ሥራ የገቡት አዳዲሶቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና የኢንቨስትመንት አዋጅ (1180/2012) ተጠቃሽ ናቸው። አዋጁ ለግሉ ዘርፍ ሰፊ የኢንቨስትመንት እድሎችን የሚከፍት ነው። በቅርቡ ይፋ የተደረገው የልዩ ኢኮኖሚ ዞኖች ፖሊሲም ተጨማሪ ማሳያ ነው።

ባለፉት ዓመታት ከ80 በላይ ለቢዝነስና ኢንቨስትመንት ሥራ ማነቆ የነበሩ ሕግጋት ተሻሽለዋል ያሉት አቶ ተመስገን፣ አዲሶቹ ሕግጋት ለኢንቨስትመንት ምቹ ከባቢ የሚፈጥሩ ቢሆኑም ለግል ባለሀብቶች በሚፈለገው ልክ ማስተዋወቅ አልተቻለም ይላሉ። ‹‹ፎረሙ በኢኮኖሚ ማሻሻያው ይፋ የተደረጉ ለውጦችን እንዲሁም ባለፉት ዓመታት የተተገበሩት የኢንቨስትመንት ከባቢ ማስተካከያ ሥራዎች ያመጧቸውን መሠረታዊ የሕግና የአሠራር ለውጦችን የሚያስተዋውቅ መድረክ ይሆናል›› ሲሉ ይገልጻሉ።

አቶ ተመስገን እንደሚሉት፣ ፎረሙ በማክሮ-ኢኮኖሚ ደረጃ የተደረጉ ማሻሻያዎች (በተለይም በቴሌኮምና በፋይናንስ ዘርፎች የተጀመሩ ሥራዎችን)፣ በዘርፍ ደረጃ የምጣኔ ሀብት እድገት ምሰሶ ይሆናሉ ተብለው የተለዩ ዘርፎች (ግብርናና የግብርና ማቀነባበሪያ፣ የማምረቻ፣ የማዕድን፣ የቱሪዝም እና የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ) እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳለጥ የተጀመሩ የዲጂታል አሠራሮች የሚተዋወቁበት የኢንቨስትመንት አቅም ማሳያ መድረክ እንደሚሆን ይጠበቃል።

ቀደም ሲል በኢንቨስትመንት ላይ ተሰማርተው የቆዩ ባለሀብቶች ሥራቸውን በማስፋት አዳዲስ የኢንቨስትመንት አማራጮችን እንዲመለከቱ ፎረሙ የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር ባለሀብቶቹ ከፖሊሲ አውጪዎችና ውሳኔ ሰጪ የመንግሥት አካላት ጋር በሚኖሯቸው ግንኙነቶች ስለሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች በቅርበት ለመወያየትም እድል ይፈጥራል። ከዚህ በተጨማሪም ፎረሙ ክልሎች ያሏቸውን የኢንቨስትመንት አማራጮች ለባለሀብቶች የሚያስተዋውቁበት መድረክም ይሆናል። የቢዝነስ ተቋማት እርስ በእርሳቸውና ከመንግሥት አካላት ጋር የሚገናኙባቸው መድረኮችንም ያካትታል።

በፎረሙ ላይ በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ከ600 በላይ አዳዲስና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል። እስካሁን ድረስ 500 ባለሀብቶች ተመዝግበዋል። ሚኒስትሮችና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት በሚገኙበት የሚካሄዱ ከፍተኛ የፓናል ውይይቶችን (High Level Panel Discussions) ጨምሮ፣ የኢንቨስትመንት አማራጭ ማስተዋወቂያ እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች፣ የልዩ የኢኮኖሚ ዞኖችና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ጉብኝቶች፣ ኤግዚቢሽኖችና ተዛማጅ መርሃ ግብሮች ይካሄዳሉ። ከወሳኝ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ከዚህ ቀደም ከኮሚሽኑ ጋር ግንኙነት ከነበራቸው አካላት ጋር የመግባቢያ ስምምነቶች ይፈረማሉ። ይህን ለማሳካትም ልዩ የኢንቨስትመንት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው በሚታሰቡ አገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ምልመላዎችን እያካሄዱ ናቸው።

በፎረሙ ላይ ከ50 በላይ ከፍተኛ የፌዴራልና የክልል ባለስልጣናት ይገኛሉ። የሥራ ኃላፊዎቹ በየዘርፎቻቸው ያሉ እድሎችን በማስተዋወቅ እንዲሁም ለባለሀብቶች ጥያቄዎች ቀጥተኛ ምላሽ በመስጠት ይሳተፋሉ። ከዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ኤጀንሲዎች ማኅበር የሚመጡ ተወካዮች ደግሞ ስለዓለም አቀፍ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት አቅጣጫዎች ገለፃ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ስመ ጥር የሆኑ የቢዝነስ ተቋማት ሥራ አስፈፃሚዎችም ልምዳቸውን ያካፍላሉ። ከዚህ በተጨማሪም ሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የየራሳቸውን ቦታ ወስደው ያሏቸውን አማራጮች በሰፊው የሚያሳዩበት እድል ይኖራቸዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስትመንት ፎረሙ ሦስት ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የመነሻ መድረክ ይሆናል ብሎ ይጠበቃል። በመሆኑም ቀጣዩ የአውሮፓውያን ዓመት እስከሚገባ ድረስ ሦስት ቢሊዮን ዶላር ተጨማሪ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

አቶ ተመስገን ባለፉት ዓመታት በተሠሩት የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ ሥራዎች ከተመዘገቡ ስኬቶች በተጨማሪ ኢትዮጵያ ያሏትን ዘርፈ ብዙ የኢንቨስትመንት አማራጮች በማየት በራሳቸው ተነሳሽነት ወደ አገሪቱ መጥተው በኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ በርካታ የውጭ ኢንቨስተሮች መኖራቸውን ጠቅሰው፣ ‹‹ኢንቨስት ኢትዮጵያ›› ፎረም በቀጣይ ዓመታት እያደገ እንዲሄድና በአፍሪካ ደረጃ ተጠቃሽ የሆነ የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ፎረም እንዲሆን ጥረት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

መሰል የኢንቨስትመንት አቅም ማስተዋወቂያ መድረኮች ኢንቨስትመንትን ለማነቃቃት ትልቅ ሚና እንዳላቸው ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚሳዩ የምጣኔ ሀብት ምሁራን ያስረዳሉ። በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁ ‹‹በምጣኔ ሀብታቸው ያደጉ አገራት ጭምር እንዲህ ዓይነት የኢንቨስትመንት አቅም ማስተዋወቂያ መድረኮችን የኢንቨስትመንት ዘርፋቸውን ለማሻሻል ይጠቀሙባቸዋል።›› ሲሉ ይገልጻሉ። ‹‹ብዙ አገራት የኢንቨስትመንት አቅሞቻቸውን የሚያስተዋውቁባቸውን መድረኮች በተደጋጋሚ ሲያዘጋጁ ማየት የተለመደ ነው። መድረኮቹ አገራት ያላቸውን አቅም በትክክል ለማሳየት ይጠቅማሉ። ስለሆነም ፎረሙ ለአገሪቱ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ማደግ የሚኖረው ሚና የሚያጠያይቅ አይደለም›› ይላሉ።

እንደሳቸው ማብራሪያ፣ የውጭ ባለሀብቶች በተለይም ስለአፍሪካ ያላቸው ግንዛቤ በቂ ስለማይሆን መሰል የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ማዘጋጀት እጅግ አስፈላጊ ነው። እነዚህ መድረኮች ግንዛቤ በመፍጠር ባለሀብቶች ወደ ኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲሰማሩ ያመቻቻሉ። ‹‹ኢንቨስት ኢትዮጵያ›› ፎረምን በታቀደለት ዓላማ መሠረት በመምራት የኢንቨስትመንት ዘርፍ አቅምን ማሳደግና ተጨማሪ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን መሳብ ይገባል።

ዶክተር ሞላ ፎረሙ ተጨማሪ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ጠቁመው፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በዘላቂነት ለማሳደግ ሰላምና ፀጥታን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስፈን እንደሚገባም ገልፀዋል። እንደ ‹‹ኢንቨስት ኢትዮጵያ›› ያሉ ፎረሞችን ከማዘጋጀት ባሻገር ሰላምና ፀጥታን በዘላቂነት በማስፈን፤ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት መጠን እና የተሳትፎ መስክ በማስፋት የዕውቀት፣ የክህሎት፣ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ስርጸትን ማፋጠን ተገቢ ይሆናል ብለዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ በአጠቃላይ በውጭ እና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል ትስስርን በማስፋት፣ የኢንቨስትመንት ክልላዊ ስርጭትን በማሻሻል፣ እንዲሁም የውጭ ካፒታል በመጠቀም የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ተወዳዳሪነት በማሳደግ፤ ኢንቨስትመንቶች በአገራዊ የኢንቨስትመንት ዓላማዎች የተመለከቱ ግቦችን ማሳካታቸውን ይገባል። እንዲሁም በሕግ አግባብ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት፣ ኢንቨስትመንት የሚመራበትን ሥርዓት ይበልጥ ግልጽ፣ ተገማች እና ቀልጣፋ እንዲሆን በማድረግ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠንና የእድገቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ ይገባል።

# ጎሜ

# ቆሻሻ እና እኛ

ግርማ መንግሥቴ

ለዚህ ጽሑፍ ይህንን ርእስ በስያሜነት ስንሰጥ ብዙ አስበንበታል። እናስብ ዘንድ ያደረገን ደግሞ "ማ ይቅደም?" የሚለው ሲሆን፣ ሄዶ ሄዶ እንደምንመለከተው "ቆሻሻ" የመሪነት ስፍራውን ይዟል። የዚህ ምክንያቱ ብዙ የሚያነጋግር ቢሆንም ለጊዜው ትተነው እንለፍና "ቆሻሻ እና እኛ"ን ወደተመለከተው ጉዳያችን እንገስግስ። "ከአፍሪካ የመጀመሪያው ..." የሚለው ጎልቶ በሚቀነቀንባት፤ አንድም ቦታ "ከአፍሪካ ቀዳሚዋ ..." ተብሎ በገለልተኞች ባልተረጋገጠላት አዲስ አበባ ማሳያም እንቆዝም።

## እንደ መግቢያ

አለማችን በአመት በአማካይ 2.01 ቢሊዮን ቶን ደረቅ ቆሻሻን "ታመርታለች"። ከዚህ ውስጥ 33 በመቶ የሚሆነው ለሰውና አካባቢ ጠንቅ በሆነ ሁኔታ ነው የሚወገደው። እንዲሁም፣ አለማችን በአማካይ በቀን 0.74 ኪሎግራም (ይህ ከ0.11 እስከ 4.54 ኪሎግራም ድረስ የሚሄድ ነው) ቆሻሻን ትታቀፋለች። ይህንን የሚነግረን በ2018 የተደረገ አለም አቀፍ ጥናት ነው። "ከዚህ ውስጥ የእኛ ድርሻ ስንት ይሆን?" ለሚለው "እኛ እዚህ ውስጥ ምንም ድርሻ የለንም" የሚል መልስ እንደማይኖረው ሁሉ፣ ለዚህ ጥያቄም እስካሁን የተሰጠ ምላሽ የለም።

"አንድ ምርት ከአሁን በኋላ የማይጠቅም ወይም የተመረተበት ተመሳሳይ ተግባር ከሌለው ቆሻሻ ይሆናል፡፡" የሚለውን ይዘን ወደ ፍተሻ ስንገባ፤ በአለማችን በየአመቱ 380 ሚሊዮን ቶን ፕላስቲክ ይመረታል። ከዚህ ውስጥ 8 ሚሊዮን ቶን የሚሆነው (plastic waste) ወደ አደባባይና ውቅያኖሶች ይጣላል የሚለውን እናገኛለን።

በአለም ላይ ያለው የቆሻሻ መጠን በየጊዜው ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይታይም። በ2050 አለማችን ቆሻሻዋ (Waste generation) ከ70 ፐርሰንት በላይ የሚጨምር ሲሆን፣ ከ3.4 ቢሊዮን ሜትሪክ ቶን በላይ የቆሻሻ መጠንም ልታስተናግድ ከወዲሁ ዝግጅቷን እያጠናቀቀች መሆኗን የwww.statista.com "Global waste generation - statistics & facts" በሚል ርእስ ያወጣው መረጃ ያመለክታል። ለዚህ የሚዳርጓትን ምክንያቶችም የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የከተሜነት መስፋፋት፣ እንዲሁም የሰዎች የሸቀጦች ግብይትና የሱቅ ሸመታ እየጨመረ መሄድና ልማድ (የአኗኗር ዘይቤ) መሆን በማለት ይዘረዝራቸዋል። እንዲሁም፣ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቆሻሻን የማስተናገድና አገልግሎት የመስጠት (waste treatment and disposal services) አቅምና ፍላጎታቸው ቀሽም መሆኑንም ሳይሰስት የዘረዘረ ሲሆን፤ እኛም ሳንሰስት እዚህ ደግመነዋል።

እንደ ጥናቱ ዳሰሳ ከሆነ በየአመቱ በሚሊዮን ቶኖች የሚቆጠር ቆሻሻ ወደ አለማችን የሚጣል ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከ20 በመቶ በታች የሚሆነው ብቻ ነው በእንደገና ጭፍለቃ ወደ ሌላ ምርት ተቀይሮ አገልግሎት የሚሰጠው። ሌላው፣ እኛ "ቆሼ" እንደምንለው አይነት ስፍራ (landfill sites) እየተወሰደ ነው የሚጣለው። በኋላስ? በኋላማ፣ ቆሼ እኛ ላይ ያደረሰውን ማስታወስ ነዋ።

የቆሻሻ ጉዳይ የዘመኑ አደገኛ ጉዳይ መሆኑን የሚገልፀው ይህ ጥናት አለማችንን በሁለት የቆሻሻ ጎራዎች ከፍሎ የሚያይ ሲሆን፣ እነሱንም ደሃና ሀብታም አገራት ሲሆኑ ሀብታሞቹ አገራት ከደሃዎቹ የበለጠ ቆሻሻ ቢያመርቱም ቆሻሻን የማስተናገድ ልምድ ያላቸው በመሆኑ በቀላሉ የሚያስወግዱት መሆኑን ይገልፃል። (worldatlas.comም ጉዳዩን በአገራት በታትኖ የሚያብራራ ሲሆን፣ ድረ-ገጹን መጎብኘቱ ለተሻለ ግንዛቤ ያግዛል ብለን እናምናለን።)

የአካባቢ ብክለትን ከፕላስቲክ አኳያ (plastic pollution statistics) የሚመለከተውና (በሴፕቴምበር 21፣ 2021 ጥናቱ) ወቅታዊ መረጃን ለህዝብ ተደራሽ የሚያደግውና "በ2050 በአለማችን 937 ሚሊዮን ቶን የፕላስቲክ ምርቶች ይኖራሉ፤ በአሁኑ ሰአት በአለማችን ካሉት የፕላስቲክ ምርቶች ከ90 በመቶ በላይ የሆኑት ሪሳይክል አይደረጉም" የሚለው ድርጅት እንደሚነግረን ከሆነ በአለማችን 8.3 ሚሊዮን ቶን ፕላስቲክ በአለማችን የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 6.3 ቢሊዮን ቶን የሚሆነው ለሰው ልጅ ጤና ጠንቅ በሆነ መልኩ የሚገኝ ነው።

እንደዚሁ ጥናት ከሆነ፣ በ2050 በአለም ላይ በሚገኙ ውቅያኖሶች ሁሉ ከአሳዎች ቁጥር ይልቅ የተጣሉ ፕላስቲኮች ቁጥር በበርካታ እጥፎች የሚበልጥ ይሆናል። ጉድ በል ጎንደር አለ።

በአመት 42 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ፕላስቲክ የምታመርተው አሜሪካ ሳትቀር፣ 1 ሚሊዮን ቶን ያህሉን ወደ ውቅያኖሶች በመጣል ለችግሩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገች ትገኛለች። ጉድ በል በጌምድር ይሏል ይሄኔ ነው። (እኛ 101ኛውን የፕላስቲክ ውሃ አምራች ፋብሪካን በቅርቡ ስለማስመረቃችን እንጂ ሌሎች፣ እዚህ እየተነጋገርንባቸው ያሉ መረጃዎችን በተመለከተ የነገረን ባለመኖሩ ስለ ሰው ጉድ (ባለቅኔው "ምናልባት ቢያስፏጨው ...) እንዳለው፣ ቢያስፏጨን በማለት) ማውራቱን መርጠናል።)



በቆሻሻ ብዛትና ብክለት ፊሊፒንስን 1ኛ፣ ኢንዶዥያን 2ኛ፣ ብራዚልን 3ኛ . . . ያደረገው የ2023 ጥናት ወደ እኛ አልመጣም እንጂ ቢመጣ ኖሮ የፊሊፒንስን ቦታ ለኢትዮጵያ አይሰጥም ማለት አይቻልም ነበር። (በ2021 በተደረገ ጥናት፣ በአመት 540,000 ቶን ፕላስቲክ የምታመርተው ኖርዌ ከ97 በመቶ በላይ ሪሳይክል በማድረግ አለምን እየመራችና Norway the highest recycling country for plastic. እየተባለላት ይገኛል።) በ2022 ጀርመን 66.1% የሚሆነውን በዳግም ጭፍለቃ መልሳ ወደ ስራ በማስገባት ከአለም 1ኛ በመሆን አለምን እጇን ከንፈሩ ላይ አስጭናለች። ኢትዮጵያ እንዲህ የሚባልላትን ጊዜ መናፈቅ ይቻላልን?? ከተቻለስ፣ መቼ??፡፡

እንደሚታወቀው ቆሻሻ እና እኛ የተለያየንበትን ጊዜ መናገር እጅጉን ይከብዳል። "መች ተገናኝተን የምናውቀውን ነው . . .?" የሚል አስተያየት እንደማይነሳው ሁሉ፣ "መች ተለያይተን የምናውቀውን ነው . . .?" የሚል አስተያየትም ሊያስነሳ ይችላል። ለማንኛውም ክርክሩ መሬት ያለውን እውነታ አይፍቀውም እና ወደ ተነሳንበት እንሂድ።

ያገለገሉና ማገልገል ያቆሙ የቤት እቃዎችን ከቤት ማስወገድ በማይሆንላት አገር፤ ያገለገሉ ፕላስቲክ ጠርሙሶችና ሌሎች ለአዲስ ገበያ ፍለጋ በይፋ ወደ ክፍለ አገራት (ለዛው፣ ለፈረደበት የገጠር ሕዝብ) የሚላኩባት ብቸኛ አገር ኢትዮጵያ . . .፤ በቆሻሻ የተነሳ የበርካቶች ሕይወት የተነጠቀባት አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ስትሆን፣ ከከተሞችም አዲስ አበባ ነች። "ታዲያ ምን ትምህርት ወሰደች?" ብሎ የሚጠይቅ ካለም መልሱ የሚሆነው "ምንም" ነው። ምንም . . .። በመሆኑም ዝናም ጠብ ባለ ቁጥር ከየቱቦው እየተግተለተለ የሚወጣው የቆሻሻ በየአይነቱ አይን ያስቆረጥማል ብቻ ሳይሆን አፍንጫ ሳይቀር ያሰንጋል።

በአዲስ አበባ ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ዘነበወርቅ፣ ጉልት፣ ቀጫ ሰፈር፣ ሰማኒያ አራት፣ ቻይና ካምፕ፣ ቆሬ፣ ጉድ ሼፐርድ፣ ወድቆ የተነሳ፣ ገብረክርስቶስ፣ ጎንደር ሰፈር፣ ፈረንሳይ ሰፈር፣ ሀምዛ ማህበር፣ ቄሶች ሰፈርና በመሳሰሉ መንደሮች (ሄኖክ በመጣጥፉ እንደዘረዘረልን) ወደ ተከበበውና (ለቆሼ ራስጌውን የሰጠው ጉድ ሼፐርድም ሆነ በደርግ የመጨረሻ ሰዓት በምሪት የተዘረጋው እንደ ሀምዛ ማህበር እና ቄሶች ሰፈር ያለው ማህበር ቤት ሕገወጥ መንደር ሳይሆን በከተማችን ከሚገኙ ቀደምት ሰፈሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው) ቆሼ እሚባለው አካባቢ የደረሰውን የከፋ አደጋ (ቅዳሜ ምሽት መጋቢት 2/2009 ዓ.ም.)፤ በአደጋው ምክንያትም የሞቱትን ሰዎች እና የወደመውን ንብረት ማንም አይረሳውም።

በብዙ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ ቆሼን የኑሮ መሰረት አድርጎ ሲኖር ቻይና ቀለበት መንገድን ሲሰራ ከተፈጠረው የስራ እድል ውጪ አዳቾም ህይወቱን የሚደጉምበት የኑሮ መሰረት ያልታሰበለት ነበር፡፡ ይሄ የሶስት መንግሥት ድምር ውጤት ዛሬ "ቆሼ ተደርምሶ ወገኖቻችን አለቁ" ለሚለው መራር ዜና አበቃን በማለት የትውልድ ስፍራው ዘነበ ወርቅ አካባቢ የሆነው፣ የድሬ ቲዩብ ሔኖክ ስዩም ማስነበቡ የሚታወስ ነው፡፡ እንግዲህ፣ እያወራንለት ያለው አጅሬ ቆሻሻ መጠነ ጥፋቱ ታሪካዊና እዚህ ድረስ ነው ማለት ነው።

ቆሼ በወቅቱም "ወይ ቆሼ ምግባችንም ሞታችንም አንተው ትሆን" ተብሎለት በነበረው ስፍራ ላይ የደረሰው አሳዛኝ እልቂት ምክንያቱ የቆሻሻ ተራራ መናድ መሆኑ ቢታወቅም ለቆሻሻው ተራራ መናድ ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ ግን በወቅቱ ግልፅ የሆነና በህጋዊ ምንጭነት ሊጠቀስ የሚችል መልስ የተሰጠበት አጋጣሚ አልነበረም።

በወቅቱ "በአደጋው የሞቱ ሰዎች ቁጥር ዛሬም 113 እንደሆነና ፍለጋውም እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡ የአደጋውን መንስዔ እስከዛሬ ማወቅ እንዳልተቻለ ገልፀው ይሕንን የሚያጣራ እና የሚያጠና ቡድን ከሀገርና ከውጭ ሀገር ባለሙያዎች" መዋቀሩን የከተማው መስተዳድር ቢነግረንም ምን ላይ እንደ ደረሰ እስካሁን ያወቅነው ምንም ነገር የለም።

ይህ እንግዲህ የቆሻሻ እና የእኛን ታሪካዊ ዝምድና የኋሊት ለማስታወስ የተደረገ መንደርደር ሲሆን ወደ አሁናችን ስንመጣ ደግሞ የሚከተለውን እናገኛለን።

የዛሬዋ ኢትዮጵያ፣ በተለይም ከተሞቿ ከወትሮው ለየት ከሚሉባትና "ይበል" ከሚያሰኙ ተግባራት መካከል የፅዳት ስራዎች ይገኙበታል።

መንግሥት ጥሩ ስራ ሰርቷል ካልን ልንጠቅስለት ከሚገቡት ተግባራቱ መካከል የአካባቢ ፅዳት ስራዎችን ባለቤት ኖሯቸው እንዲሰሩ ማድረጉ ይመስለኛል። አዎ፣ ዛሬ በየትኛውም የአዲስ አበባ አካባቢ፣ ሰፈርና መንደር በፅዳት ሰራተኞች አማካኝነት የፅዳት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ድሮ እዛና እዚህ በተቀመጡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች አማካኝነት ብቻ ይሰበሰብና ወደ ቆሼ ይጣል የነበረው የመዲናዋ ቆሻሻ ዛሬ በየመንደርና ሰፈሩ እለት በእለት እየተጠረገ፣ በማዳበሪያም እየተሰበሰበና እየተሞላ ወደ'ሚሄድበት እየሄደ ይገኛል። የግሉ ዘርፍ ተሰማርቶ ቆሻሾችን ሲያነሳ እየተመለከትን ነው። አስፓልቶች እየተጠረጉ ናቸው። ችግር ያለው ግን ሌላ ነገር ነው።

ከላይ ያልነው እንዳለ ሆኖ ችግር የሚለው ነገር የፅዳት ሰራተኞች ቤት ለቤት እየሄዱ፣ በር እያንኳኩ "የቆሻሻ ያለህ" በሚሉበት በዚህ ዘመን፣ ሰፈርና አካባቢያችንን እናፅዳ ተብሎ ወደ ስራ በተወጣበት በዚህ ወቅት፣ የመንግስት በጀት ተመድቦና የሰው ኃይል ተሰማርቶ ቆሻሻ ከየአካባቢው በሚመነጥርበት በአሁኑ ሰአት፤ የግል ባለሀብቶች ሳይቀሩ በፅዳት ስራዎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ በጀመሩበት 21ኛ ክፍለ ዘመን የቤትና የአካባቢ ቆሻሾችን በእነዚህ አካላት አማካኝነት ማስወገድ ሲገባቸው በየቱቦውና መንገዱ፣ የፅዳት ሰራተኞች ከሄዱ በኋላ በያገኙበት የሚጥሉ ሰዎች የመኖራቸው ጉዳይ ነው።

ጉዳዩን ጥያቄያዊ እናድርገውና ለምንድን ነው ሰዎች በየቱቦው፣ በየመንገዱ፣ በየአጥሩ . . . ላይ ቆሻሻ የሚጥሉትና አካባቢያቸውን ላልተፈለገ ጉስቁልና የሚዳርጉት? ለምንድን ነው በማዳበሪያ አድርገው ለፅዳት ሰራተኞች ምቹ አድርገው በመጠበቅ አካባቢያቸውን ደህንነቱ የተጠበቀ የመኖሪያ ስፍራ የማያደርጉት? የምን ልክፍት ነው? ሳይቸግር ጤፍ ብድር ውስጥ በመግባት ለጤና ጠንቅ በሆኑ ተግባራት ላይ የሚጠመዱት? ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ ምን ይሆን?

ይህንን አባባል መሬት አውርዶ ለማየት ከተፈለገ ትንሽ ዝናብ ጠብ ሲል የአዲስ አበባ መንገዶችን ማየት ነው። ጎርፍ አግተልትሎ የሚያወጣው የቆሻሻ አይነት አለን? የፌስታል፣ የጫት እንጨቱ፣ የሀይላንድ (ፕላስቲክ ጠርሙሱ) መአት ተቆጥሮ ያልቃል? ምን የማይታይ የቆሻሻ አይነት (ኦርጋኒኩም (ከህያዋን የመጡ ለምሳሌ - ቅጠሎች፣ ቅርንጫፎች፣ የፍራፍሬ እና የእንቁላል ቅርፊቶች፣ የእንስሳት አጥንቶች፣ ወዘተ)፣ ኦርጋኒክ ያልሆነውም አለ? ምንስ አይነት የማይለቀቅ ሸንት ቤት አለ? ምንም የለም።

## ቤሳስ?

ሌላ ጉድ (ጉድ የሚገልፀው ከሆነ) ለማየት የሚፈልግ ካለ በአካባቢው ከሚገኝ አንድ ትንሽ ዘለግ ያለ ፎቅ ይፈልግና እዛ ላይ ወጥቶ ቁልቁል ይመልከት። በቃ፣ መሬት ላይ የድንጋይ እጥረት የተፈጠረበት ምክንያት እስኪገለፅለት ድረስ የእኛና የቆሻሻ ታሪካዊ ትስስር እስከበቃው ይወጣለታል። ለመሆኑ፣ ጣሪያችን ቆርቆሮ ነው፣ ወይስ ቆሻሻና ድንጋይ??

የዚህ ሁሉ ችግር ዋናው መዘዝ ግዴለሽነትና ከቆሻሻ ጋር አብሮ የመኖር ልምድ መኖር ነው የሚሉ በርካቶች ናቸው። ባይሆን ኖሮ የፅዳት ሰራተኞች በየ በር ላይ እየመጡ "የቆሻሻ ያለህ"፣ "ቆሻሻ አውጡ" ሲሉ አውጥቶ ለእነሱ ማስረከብ ባልከበደም ነበር። ቆሻሻውን ወስዶ በየመንገዱ ዳር ዳር እተቀመጡት ማዳበሪያዎች ውስጥ መክተት ባላስቸገረም ነበር። ሌላው ሁሉ ቢቀር እንኳን ለፅዳት ሰራተኞቹ ምቹ የሆኑ ቦታዎች ላይ ወስዶ ማስቀመጥም እንደ ነውር ባልተቆጠረም ነበር።

"ሁሉም ሰፈሩን ቢያፀዳ ፓሪስ በአንድ ቀን ትፀዳ ነበር" የሚለው እድሜ ጠገብ አባባል ለአዲስ አበባም ሆነ ሌሎች ከተሞች ይሰራል እኮ። በፓሪስ አስታኮ ተነገረ እንጂ አገልግሎቱ ሁሉንም ማስተማር ነው። ሁሉም ከተሞች ፅድት ብለው ማየት ነው። ከተሞች ሁሉ ለሰው ልጆች ጤናና አጠቃላይ ህይወት ምቹ ይሆኑ ዘንድ መሻት ነው። ስለዚህ ለፓሪስ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ይሰራልና ሁሉም ሰፈሩን ቢያፀዳ . . .

ዛሬ ስልጣኔ ከሚለካባቸው ጉዳዮች አንዱ ፅዳት ነው። ፅድት ያለ አካባቢ የመኖር መብትም የሰዎች የሰብአዊ መብት አካል ከሆነም ቆይቷል። ባይሆን ኖሮ ደቡብ አፍሪካዊቷ ኬፕታዎን ከአህጉሪቷ ፅድት ያለች ከተማ ተብላ 1ኛ ባልወጣች፤ የታንዛኒያዋ ስቶን ታዎን (Stone Town)ም ባልተከተለች፤ የሞሮኮዋ ማራካሽም ባልሰለሰች ነበር። እነዚህና ሌሎች የአፍሪካ ከተሞች ይህንን ማእረግ ሊጎናፀፉ የቻሉት በነዋሪዎቻቸው አፍቃሬ ፅዳትና ስራዎቻቸው አማካኝነት ነውና አዲስ አበባ ለዚህ የምትታደልበትን ዘመን መናፍቅ እንደማያሰኝ ከወዲሁ መናገር ይቻላል።

## ሳይንሳዊ አወጋገድ

እስካሁን ያወራነው ስለ ቀላሉና ማንኛችንም ልናደርገው ስለምንችለው የቆሻሻ አወጋገድ ስርአትና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ዘዴ ሲሆን፣ ሳይንሳዊውን ስንመለከት ደግሞ የሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን።

ቀደም ሲል ጠቃሚ ሕይወታቸውን ያገኙ እና ዓላማቸውን ያሟሉ ምርቶች፤ ወይም ቅሪቶች የሚሄዱባቸው በርካታ መንገዶች አሏቸው፡፡ የመጀመሪያው ለመቅበር ወደ ቆሻሻ መጣያ ቦታ መሄድ ነው፡፡ ሁለተኛው የድምፅ መጠን መያዙን ለማቆም በማቃጠያ መሳሪያ ውስጥ መቃጠል ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ በምርቶቹ የሕይወት ዑደት ውስጥ እንደገና እንዲካተት፤ እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ከዚህ አኳያ የአገራት ልምድ ምን ይመስላል?

"የዲ.ሲ. የህዝብ አገልግሎት ሥራዎች መምሪያ (DPW) የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ አስተዳደር ቆሻሻ እና ሪሳይክል የሚደረጉ ስብስቦችን፣ የንጽህና አጠባበቅ ትምህርትና አፈጻጸሞች፣ ያረጁ ምልክቶችን ማስወገድ፣ የህዝብ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች፣ የረገፉ ቅጠላ ቅጠሎችን መሰብሰብ እና የውስጥ መንገድና አስፋልት ጠረጋዎችን የሚያካትቱ ስራዎችን በየቀኑ የሚያከናውን" መሆኑን "ለጠቅላላ እውቀት"ና ልምድ ልውውጥ በማሰብ እዚህ ልንጠቅሰው ወደድን። በጃን. 13 2023 የተለቀቀ ጥናት በፕላስቲክ ቆሻሻ አስተዳደር በpay-to-dispose rubbish policy የምትመራው.ስዊዘርላንድ ከአለም 1ኛ መውጣቷን ማስነበቡንም እንደዛው። ቸር እንሰንብት!!!

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ዘለሰኛና ሰሞነ ሕማማት

መልካምሥራ አፈወርቅ

እየሱስ ክርስቶስ የአዳምን በደል ለመሻር ከሰማየ፣ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰላሳሦስት ዓመታትን በምድር ሲያስተምር ኖረ። ጊዜው ሲደርስ በራሱ ፈቃድና በአይሁድ ክፋት ከፍ ያለ መከራን ሊቀበል፣ ከመስቀል ተቸንክሮ ሊሰቀል ግድ ሆነ። ሞት የማይቀርለት ዕዳ ሆኖም ለሰውልጆች ሀጢያት ሲል ራሱን አሳልፎ ሰጠ። በዕለተ ዓርብ ነፍሱ ከስጋው ተለይታ ወደ መቃብር ወረደ።

እነሆ በዚህ ቀን ከፍ ያለ ኀዘንና ለቅሶ ሆነ። ምድር ተንቀጠቀጠች፣ ቀኑ ጨለመ፣ መጋረጃዎች ለሁለት ተሰነጠቁ። የክርስቶስን ሞት ያዩ ሁሉ አንገታቸውን ደፉ። በእርሱ ላይ ግን የአብ አባቱ ቃል ፈጽሞ አልተሻረም። በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል ነስቶ፣ መቃብር ፈንቅሎ ለዓለም ሕያው ሆነ።

በሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ የክርስቶስን ከሞት መነሳት እንደማየት የሚያስደስት እውነት የለም። ይህ ቀንም ዕለተ ትንሳኤ ወይም ፋሲካ ተብሎ ይጠራል። ጌታ እየሱስ ክርስቶስ መከራና ስቃይ የተቀበለባቸው ቀናት «ሰሞነ ሕማማት» ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ጊዜያት «ሰሞነ ከሚለው ቃል ተዋደው ሳምንቱን ወይም ስምንቱን ቀናት በማስታወስ ስድስቱን የስቃይና መከራ ቀናት የሚያመላክቱ ናቸው፡ ፡«ህመ» የሚለው ቃል በግዕዝ «ታመመ» የሚለውን ፍቺ ይይዛል።

እየሱስ ክርስቶስ ወደእየሩሳሌም ከገባ አንስቶ ከትንሳኤው ቀናት በፊት ያሳለፋቸው የመከራ ቀናት የመጨረሻ ሳምንት «ሰሞነ ህማማት» ተብሎ ይጠራል። ይህ ሳምንት ክርስቶስ የበረከተ ችግርና መከራ፣ ስቃይና አበሳ የተቀበለበት ነውና ህመሙ በተለየ ሁኔታ ይታወስበታል።

የመስቀሉ ህማሞች በአስራሦስት የስቃይ መገለጫዎች ይተነተናሉ። ሳዶር፣ አላዶር፣ አዴራ፣ ዳናትና ሮዳስ በተሰኙ አምስቱ ቅንዋተ መስቀል ክርስቶስ በችንካር መሰቀሉም ይገለጥበታል።

የሰሞነ ህማማት ቃል ሲፈተሽ «ሰመነ» ማለት ሳምንት አደረገ ከሚል ትርጓሜ ያደርሳል። ይህም ከዕለተ ሆሳዕና እስከ ትንሳኤ ሌሊት ያሉትን ስምንት ቀናት የሚያመላክት ነው።

«ህመ» ማለት ታመመ ማለት ነው። ይህም እየሱስ ክርስቶስ የሰውልጆችን ከዲያብሎስ የባርነት ግዛት ነፃ ለማውጣት በፈቃዱ የተቀበላቸውን የስቃይና መከራ ቀናት የሚያስታውስ ነው። የሰሞነ ህመማት ቀናት ሲታውሱ በተለየ ሥርዓትና ልማድ ነው። በነዚህ ቀናት ሕዝበ ክርስቲያኑ የክርስቶስን ውለታና ስቃይ የሚያስቡት በኀዘንና በለቅሶ፣ በጾምና ስግደት ይሆናል።

በሰሞነ ህማማት ጊዜ መስቀል መሳለም፣ የትከሻ ሰላምታን መለዋወጥ፣ በተለይም መሳሳም አይፈቀድም። እንዲህ ማድረጉ አይሁዶች ክርስቶስን ለመስቀል ከሰኞ አስከ አርብ ተሰባስበው የመከሩበትን፣ «እንስቀለው» ሲሉ የተንሾካሾኩበትን፣ በክፋት የተገናኙበትን ጊዜ ያስታውሳል።

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጠቀሰው ይሁዳ ክርስቶስን ለጠላቶቹ አሳልፎ ለመስጠት የተጠቀመው ምልክት ትከሻውን በመሳም ነበር። ይህ ዓይነቱ ሰላምታ ፍጹም ሰላም የራቀው፣ ፍቅር ያልነበረውና በተንኮል የተዋጠ መሆኑ ይታሰባል። ይህ ወቅት ፍቅር ያልታየበት፣ ሰላም ያልወረደበት፣ መልካም ጉዳዮች ያልሆኑበት ነውና ያለአንዳች ሰላምታ ጊዜውን በማሰብ ይታወሳል።

ሰሞነ ህማማት በገባ ጊዜ ሥርዓተ ቅዳሴ አይኖርም። ማንም ሰው ቢሞት ሥርዓተ ፍታት አይደረግም። አስቀድሞ ጸሎትና ፍታቱ በየቤተክርስቲያናቱ ይካሄዳል። የሃይማኖቱ አስተምህሮ እንደሚያስረዳው በዚህ ሳምንት የሰው ልጆች ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገሩበት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ያለፉበት ተምሳሌት ሆኖ ይጠቀሳል። በሰሞነ ህማማት ከሰኞ እስከ ዕሁድ ያሉት ቀናት የራሳቸውን ምስጢር ይዘው ተቀርጸዋል። በእያንዳንዳቸው ቀናት ላይ የሚያርፈው ምሳሌም በዚህ መልኩ ይተነተናል።

### ሰኞ

በዕለተ ሰኞ፡- እየሱስ ክርስቶስ «ቤቴ የእግዚአብሔር ቤት ተብላ ትጠራለች እናንተ ግን መነገጃ አደረጋችሁት» ሲል በስፍራው ሲነግዱ የዋሉትን ሰዎች የማስወጣቱን እውነት ይጠቁማል።

### ማክሰኞ

በዕለተ ማክሰኞ፡- እየሱስ ክርስቶስ ከመሰቀሉ አስቀድሞ ለመጨረሻ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ ያስተማረበትን ጊዜ ያስታውሳል።

### ረቡዕ

ዕለተ፡- ረቡዕ አይሁድ በክርስቶስ ላይ የመከሩበት ነው። ይህ ቀን መግደላዊት ማርያም እያለቀሰች የእየሱስ ክርስቶስን እግር በሽቶ ያጠበችበት ቀን መሆኑ ይታወቃል። ከዚሁ ጋር ተያይዞም ዕለቱ የመልካም መዓዛና የዕንባ ቀን በሚል ይታሰባል።

### ሐሙስ

ዕለተ፡- ሐሙስ በሌላ ስያሜው ጸሎተ ሐሙስ በሚል ይጠራል። በዚህ ቀን እየሱስ ክርስቶስ ትህትናን ለዓለም ለማስተማር ዝቅ ብሎ የሐዋርያትን እግር ያጠበበት ነው። ዕለቱን ደቀመዛሙርቱ ራት ባዘጋጁ ጊዜም ክርስቶስ አስቀድሞ ሞቱን ያውቅ ነበርና ከቀረበው ቂጣና ወይን ባርኮ «ስጋና ደሜ» ይህ ነው ሲል የሰጣቸውን እውነት ያስታውሳል።

### አርብ

ዕለተ አርብ፡- እየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች ሐጢያትና በደል በመስቀል ተቸንክሮ በታላቅ ስቃይና ሕመም የሞት ጽዋን የተጎነጨበት ቀን ነው።

### ቅዳሜ

ዕለተ፡- ቅዳሜ የእየሱስ ክርስቶስ የሞቱ ማግስት ነው። በዚህ ቀን ወደ ሲኦል ወርዶ በስፍራው ላሉት ሁሉ ሰላምን እየሰበከ ወደ ገነት ያስገባቸውን ምሳሌ ይጠቁማል።

### ዕሁድ

ዕለተ፡- ዕሁድ የእየሱስ ክርስቶስን ከሞት የመነሳት ትንሳኤ ያበስራል። ይህ ቀን ክርስቶስ ከሙታን መሀል ከፈኑን ገልጦ፣ መቃብር ፈንቅሎ፣ ሞትን ድል የነሳበት ታላቅ ዕለት ነው። ይህም ቀን በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ፋሲካ ተብሎ ይከበራል ።

በነዚህ ሰባት ሰሞነ ሕማማት የእየሱስ ክርስቶስን የጭንቅ ቀናት ለማሰብ ሕዝበ ክርስቲያን፣ ካህናትና ዲያቆናት፣ በቤተክርስቲያን አጸድ ይሰባሰባሉ። ከምግብና መጠጥ ተቆጥበውም ራሳቸውን በጾም፣ በስግደት ያደክማሉ። ውስጣቸውን በንስሀና ያነጻሉ።

በዚህ ሳምንት የእየሱስን ስቃይና መከራ በኀዘን የሚያስቡ ዜማዎች ብቻ ይደመጣሉ። ጊዜው ደስታና ጨዋታን አይፈቅድምና «ግብረ ህማም» የተሰኘ መጽሐፍ እየተነበበ ራስን ለስግደትና ጾም ማስገዛት ግድ ነው።

በዚህ ሳምንት ከሕዝበ ክርስቲያኑ አንደበት መደመጥ ያለበት ዜማ የክርስቶስን ኀዘንና መከራ የሚያስታውስ፣ ስቃይ መከራውን የሚዘክር የንስሀ መዝሙርና የዘለሰኛ ዜማ ነው።

የዘለሰኛ መዝሙሮች በአብዛኛው ከተለመዱት ስንኞች ወጣ ያሉ ናቸው። ልብ ብሎ ላዳመጣቸው ትርጓሜያቸው በብዙ ፍቺ ይገለጻል። የዓለምን ከንቱነት፣ የሰውልጆችን ማንነት በተለየ ምስጢር ይጠቁማሉ። ፈጣሪን ለማመስገንም ቅድሚያውን ይሰጣሉ እንዲህ በማለት።

**ክበር ተመስገን የኛ ጌታ፣**
**ከጠዋት አንስቶ እስከ ማታ።**
**እዛ ሳይ ሆኖ ቢጠራኝ፣**
**ወይ እንዳልሰው ድምጽ የለኝ።**
**ባልሰማ እንዲ ነው ዝምታዬ፣**
**አቤት አቤቱ ጌታዬ ።**
**በእሳት ዙፋን ሳይ ይቀመጣል፣**
**በድምጹ ምድርን ያናውጣል።**
**ሰይፍ ይመዘዛል ከአንደበቱ፣**
**እንደጌታችን ማነው ብርቱ።**
**ገጹ እንደ ፀሐይ የሚያበራ፣**
**ግርማ ሞገሱ የሚያስፈራ።**

የዘለሰኛ ግጥሞች በአንድ ትርጉም ብቻ አለመፈታታቸው አድማጩን በተለየ ጥበብ እንዲመራመር ያደርጋል። ለምሳሌ ቀጥሎ የቀረበው የዘለሰኛ ስንኝ የሰውን ከንቱነት፣ ድንገት ወጥቶ ከመቅረቱ፣ እንዲሁም ህማማትን ከህሜት ጋር በማያያዝ እንዲህ ይገልጸዋል።

**ይፍቱኝ አባቴ በጠዋቱ፣**
**ወጥቶ ቀረ ነው ሰው በከንቱ።**
**ይፍቱኝ ሳይል የበረረ፣**
**እንደታሰረ በዚያው ቀረ።**
**ቅዳሴ ቅኔ ማህሌቱ፣**
**አቤት ማማሩ አይ ውበቱ።**
**ሥራውም ቀሏል ከትናንቱ፣**
**ተጣልቻለሁ ከአባቶቼ ፣**
**የጾሙን መብዛት ጠልቼ።**
**አርባ ቀን ፃመን በነበር ፣**
**ምነው ማማቱ ቢቀር።**
**የፃም አትክልቱ፣ እልበት ሽንኩርቱ፣**
**እንደ ጥሬ ስጋ ምነው መበላቱ፣**
**እስቲ ቀንሱለት ባይሆን ስማማቱ።**
**ስጋ በእሳት ነበር የሚቀቀል ድሮ፣**
**መጥበስ ተጀምሯል በምሳስ ዘንድሮ።**
**ዓርብና ዕሮቡን ቆጥረን ብንጾመው፣**
**በማማት መብላቱን ምነው አልተውነው።**

በዘለሰኛ የአምላክ ቸርነት፣ የዚህ ዓለም ሕይወት ደጋግሞ ይሰበካል። የሰውልጅ ማንነትና የእግዜአብሔር ኃያልነት ይወሳል። ለፈጣሪ የሚቸር፣ ምስጋናና ክብር ሁሉ በስንኝ ተቋጥሮ፣ በዜማ ታጅቦ ይደመጣል።

**ትዕግስትህ ብዙ ነውና፣**
**ኃያል እግዚአብሔር ገናና።**
**ነነዌን አይተህ የራራህ፣**
**በል ስማኝ ዛሬም ስጠራህ።**
**ሰውማ ትቷል ነገሩን፣**
**በአንተ ሳይ ራስ መጣሉን።**
**መልከ ፈጣሪን የመሰለ፣**
**እንደሰው ፍጡር የታለ።**
**የእየሩሳሌም ገዳም ቄስ**
**አሜን ሲል ያድራል ሲቀደስ**
**ምን አስጨነቀው ለኛ ሰው**
**ዓለም በቃኝ ሳለው።**

አንዳንዴ በሰዎች ላይ የሚደርሰው ድንገቴ ሞት ብዙ ለሚያስብ፣ ለሚያቅደው ሁሉ ያስደነግጣል። ከምንም በላይ ግን ራስን በንስሀ አንጽቶ ላልቆየው ምዕመን ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ የማስጠንቀቂያን መልዕክት ያስተላልፋል። የዘለሰኛ ስንኝም እንዲህ ዓይነቱን እውነት በዚህ መልክ ይገልጸዋል።

**ስመኖር ስመኝ በመሬት፣**
**ንብረት አፍርቼ ልሰራ ቤት፣**
**ጥሪው ደረሰኝ በሌሊት፣**
**በከንቱ ቀረ ያሰብኩት።**
**የሰውልጅ ሲመኝ ሰፊ ርዕስት፣**
**እየመሰለው የማይሞት።**
**እልፍ የጥበብ ዘር ያስአግባብ አግብቶ፣**
**በአገልግል፣ በሙዳይ ስንት ቀለም ሞልቶ፣**
**ልቆርጠው ነው አለኝ ሳላስበው ገብቶ።**

ሞት ለሰውልጆች ሁሉ የተሰጠ ግዴታ ነው። ማንም ቢሆን በምድር ኖሮ ማለፉ፣ ጊዜው ሲደርስ መሞቱ አይቀርም። የዘለሰኛ ግጥሞችም በአብዛኛው የምድር ሕይወትንና አይቀሬውን ሞት ሳያነሳሱት አያልፉም። እየደጋገሙ እንዲህ ያወሱታል።

**ሦስት ክንድ ለክቶ ሲሰጥ በየቤቱ፣**
**እኔን ያሳዘነኝ ሁሉም መዘጋቱ።**
**ቋሚ የሚሆን ጠፋ ሰው፣**
**እየወሰደ ጨረሰው።**
**እየጣለው ሄደ እያየው አለፈ፣**
**አቤት ስንቱ ቀለም በከንቱ ረገፈ።**
**ካሰበውም ሳይደርስ በከንቱ እየቀረ፣**
**ወጥኖ ወጥኖ ስንቱ ተቸገረ።**
**እነዛ ቢሄዱ ቀድመው ከፊታችሁ፣**
**እናንተም ከኋላ ትከተላላችሁ።**

በዘለሰኛ ስንኝ መሀል ምንጊዜም ፈጣሪን ማሰብና ማወደስ የተለመደ ነው። በተለይ ደግሞ ከሞት በኋላ ለሚኖረው ሰማያዊ ሕይወት ፈጣሪን «ከሀጢያት አንጻኝ፣ ከመንግሥትህ አስበኝ፣ ይቅር በለኝ» ብሎ መማጸኑ አይቀርም። ይህ በሰውልጆች ማንነት ውስጥ የተቀረጸ እውነት ታዲያ በዘለሰኛው ቅኔ እንዲህ ተብሎ ይገለጻል።

**አምላኬ አምላኬ እያልኩህ፣**
**እኔስ በመጮህ ጠራሁህ፣**
**ከሲዖል ስቃይ ጠብቀኝ፣**
**በቀኝህ ልሁን አስበኝ።**

በአብዛኛው የሰውልጅ በምድር ሲኖር ከነፍሱ ይልቅ ለስጋው ያደላል። ይህ የዓለም እውነታም እስከዛሬ የኖረና ወደፊትም የማይቀር ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሀቅ ሲገለጽ ደግሞ ምስጢራቱ ሁሉ ከማይቀረው ሞትና ከወዲያኛው ዓለም እየተናበበ እንዲህ ይገለጻል። በመስንቆው ዘለሰኛ።

**አምላክ ግብር ጠርቶ ደግሶ ሲያበላ፣**
**ትንሹም ትልቁም ለስጋው አደላ።**
**የልደቱን በሬ ማነው ያረደው፣**
**መረረኝ እንደሬት ገና ሳልቀምሰው፣**
**መብላቴ የማይቀር ነው አሁንስ ባየው፣**
**ባገር የለም አሉ ያ ሞት ያልነካው።**

የሰለሰኛ መዝሙሮች ጠንካራ መልዕክቶች አላቸው፣ የዓለም እውነታን ገልጠው ሰውን ከራሱ፣ ሰውን ከአምላኩ ያስታርቃሉ። መልካም ምግባር እንዲኖር፣ መተሳሰብ እንዲለመድ ይጠቁማሉ። ፍቅርን እየሰበኩ፣ መከባበር፣ መዋደድ እንዲኖር ያስተምራሉ። በሚከተለው ሁኔታ።

**እርስ በርሳችን እንፋቀር፣**
**ልጆች እንድንሆን ለእግዚአብሔር።**
**ከሁሉ በላይ ፍቅር ይጸናል፣**
**ጌታም በቃሉ እንዲህ ብሏል።**
**ከአንድ መንፈስ ተወልደን፣**
**ከአንዱ አምላክ ተከፍለን።**
**ተፈጥረን ሳለ ከአንድ አባት፣**
**ከወዴት መጣ መለያየት።**

የመዲናና ዘለሰኛ ግጥሞች መልካም ድምጽን በተቸራቸው አንደበት፤ በመሰንቆ ታጅበው ሲደመጡ ልብን ያረካሉ፣ መንፈስን ይማርካሉ። በአብዛኛው የሚያሳድሩት ስሜትም ከተለመደው ዓለማዊ ሙዚቃና ዘፈን የሚያርቅ ነው። ብዙዎች እንደሚሉት የዘለሰኛ ዜማዎች የተለየ ኃይልና ጉልበት አላቸው። ሰው ከራሱ ጋር እንዲመክር፣ ከፈጣሪው እንዲገናኝ፣ የዓለምን እውነታ መርምሮ እንዲፈትሽ ያደርጋሉ።

እነሆ ዛሬ ዕለተ ሐሙስ ነው። ይህ ቀን ደግሞ «ጸሎተ ሐሙስ» ተብሎ ይጠራል። በዚህ ቀን እየሱስ ክርስቶስ ትህትናን ለዓለም ለማስተማር ዝቅ ብሎ የሐዋርያትን እግር አጥቧል። ደቀመዛሙርቱ ራት ባዘጋጁ ጊዜም ከቀረበው ቂጣና ወይን ባርኮ «ስጋና ደሜ» ይህ ነው ሲል የሰጣቸው ቀን መታሰቢያ ነው።

ቀኑ እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት በችኮላ መውጣታቸውን ለማሰብ ሲባል የሚታወስ የእስራኤላውያን ትውፊት ነው። ይህ ትውፊት እስራኤላውያን በችኮላ በወጡ ጊዜ የመንገዳቸው ስንቅ በወጉ ያልበሰለ ቂጣ፣ ንፍሮና መሰል ሆድ መሙያዎች እንደነበሩ ያስታውሳል።

ዕለቱ በተለይ በአገራችን ባሉ የኦርቶዶክስ ዕምነት ተከታዮች ዘንድ በተለየ ሥርዓት ይታወሳል። የዛሬው ቀን ዕለተ -ጉልባን ነው። በየቤቱ ስንዴና ባቄላ ተቀቅሎ ይበላል። ጉልባኑ ጨው በርከት እንዲልበት ይደረጋል። ጨው በባህሪው ውሀ ያስጠጣል። የዚህ ምሳሌም ክርስቶስ ሲሰቀል በውሀ ጥም መሰቃየቱን ለማሰብ ነው።

ለጉልባኑ የሚቀቀለው ባቄላ ቅርፊቱ ተልጦ ይከካል። የዚህ ምሳሌም አይሁዳውያን የክርስቶስን ልብስ አውልቀው ያንገላቱትን እውነት ለማሰብ ሲባል ነው። ከጸሎተ ሐሙስ ማግስት ስቅለት በዓል ነው። ይህ ቀን እንዳለፈም «ቅዳም ሹር» ይከተላል። እየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተከንችሮ ሞትን ድል የነሳበት፣ መቃብር ፈንቅሎ ህያው የሆነበት ትንሳኤም በዕለተ ዕሁድ ይበሰራል። ይህ ቀን በመላው የክርስትና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት የሚከበረው ታላቁ የፋሲካ አውደ ዓመት ነው። መልካም የትንሳኤ በዓልን ተመኘን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## አካል ጉዳተኛ አረጋውያንና የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲው ተስፋ

**ሰላማዊት ውቤ**

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ አረጋውያን አሁን ላይ ትኩረት እያገኙ መጥተዋል። በተለይም ዕድሜ እንቅስቃሴያቸውን የገደበባቸው ዜጎች በተለየ ሁኔታ ድጋፍና እንክብካቤ ሲደረግላቸው ይስተዋላል። ይህ እንደ ሀገርም ሆነ አካባቢ እጅጉን የሚያስደስትና ለሌሎች ምሳሌ መሆን ያለበት ሰናይ ተግባር ነው።

በዚህ የተቀደሰ ዓላማ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል በአቧሬ አካባቢ ነዋሪነታቸውን ያደረጉት የ70 ዓመቷ አዛውንት እማማ አበበች ዘውዴ ናቸው። እኚህ እናት የአንድ እግር ጉዳተኛ ሲሆኑ፤ በእርጅና ምክንያት እቤት ውለዋል። ቤት ሳይውሉ ግን የዕለት ጉርሳቸውን ለመሸፈን በዱላ እየታገዙ ይንቀሳቀሱ ነበር። በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ አረጋውያንን ካሉበት የከፋ አኗኗር ለማውጣት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት በተካሄደ መርሐ-ግብር ባለፉት ሁለት ዓመታት ቤታቸው የመታደስ ዕድል አግኝቷል። በዚህ እድል ተጠቃሚ በመሆናቸው የተሰማቸውን ሲገልፁም «እሰየው በላዩ ላይ ሊፈርስ የነበረው ቤቴ ታድሷል። እንደውም በአካል ጉዳተኛነቴ ምክንያት ከሌሎች አረጋውያን በተለየ ሁኔታ 'ቅድሚያ ይሰጣት' ተብሎ ነው የታደሰልኝ። የምበላውም አግኝቻለሁ» ይላሉ።

በፊት ቤታቸው በማፍሰሱ ብቻም ሳይሆን ከታችም የክረምት የጎርፍ መተላለፊያ የነበረ በመሆኑ ሲቸገሩ ኖረዋል። ዕድሜ ተጭኗቸው እግርና እጃቸው እንደልብ አልንቀሳቀስ ስላላቸው ጾም ውለው ያድሩ ነበርም። ቤታቸው በሴቶችና ማህበራው ጉዳይ የቁሳቁስ ድጋፍና በበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ታድሶላቸው በጥሩ ሁኔታ መኖር ሲጀምሩ ግን ሁሉ ነገር ተቀየረ። ቤታቸው በደስታ ተጎበኘም።

ቤታቸው ከታደሰ ጀምሮ "የደሀ ደሀ" በሚል በቀበሌ ተመልምለው የአንድ ሺህ ብር ድጋፍ ያገኛሉ። እናም ይህንን ሁኔታ ሲያስረዱ «አሁን በቀሪ ዕድሜዬ ፈጣሪዬን እያመሰገንኩ የምገፋበት ሁኔታ ላይ ነኝ» በማለት ነው።

«ሁለት እግሬ ጉዳተኛ ነው። በሁለት ክራንች ነው የምሄደው» የሚሉት አባት አረጋው ቶማስ ቶላም የዚህ እድል ተጠቃሚ ናቸው። ዕድሜ ተጭኗቸው መንቀሳቀስ ባቃታቸው ወቅት የመንግስት ሠራተኛ የሆኑ ጓደኛቸው ይደግፏቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። ይሁንና ይህ እስከመጨረሻው የቀጠለ አልነበረም። ጓደኛቸው በ60 ዓመታቸው ጡረታ በመውጣታቸው እጅ አጠራቸውና እሳቸውን መደጎም ቀርቶ በጡረታ የሚያገኘዋት ጥቂት ብር የራሳቸውንም ወጪ አልሸፍን ስላለቻቸው ድጋፋቸውን አቆሙ። በዚሁ ምክንያትም ወደ ልመና ወጡ። መቄዶኒያ ለመግባትም ጥረት አድርገው "ቤተሰብ አለህ" በሚል ምክንያት አልተሳካላቸውም።

"ሰው ሲሸመግል አስታዋሽ ያጣል። ብዙ ጊዜም ጡረታ ከወጣ በኋላ የሚጠቅም ፍጡር ተደርጎ አይታሰብም" የሚሉት ባለታሪካችን፤ ጓደኛቸው በጊዜው እኔ ነኝ ካለ ጎረምሳ የበለጠ የጉልበትም ሆነ ሌላ ማንኛውንም ሥራ የመሥራት አቅም ስለነበራቸው በአንድ ቀበሌ ፈቃደኝነት በኮንትራት ጥበቃ ሥራ በመቀጠራቸው የአቅማቸውን ያግዟቸው ነበር። በዚህም ልመና እንዳቆሙ ይናገራሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ደጋፊ ጓደኛቸው በሞት ተለዩዋቸው። ስለዚህም ምርጫ ስላልነበራቸው ተመልሰው ወደ ልመና ወጡ። ይህም ፈታኝ ነበር። ምክንያቱም ደግፎ ወደ ውጪ የሚያወጣቸውን ይሻሉ። ይህንን ያዩ የአካባቢው ወጣቶች ደረሱላቸውና ታደጓቸው። እራሳቸውን ችለው ባይሄዱም መሥራት ይችሉ ነበርና ወጣቶቹ "አንዲ ማማ" ከተባለ የግል ድርጅት ጋር በመነጋገር የተለያየ ሥራ እንዲሰሩ አደረጓቸው። በሥራው ጉልበታቸው መጠንከሩንም ያወሳሉ። ይሄ ድርጅት በወር 1ሺህ 500 ብር ደሞዝ ይከፍላቸዋል። አሁንም መሥራት ተሰናቸውም ቢሆን ድርጅቱ የዕለት ጉርሳቸውን አልነፈጋቸውም።

በሴቶችና ሠራተኛና ማህበራው ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች የአድቮካሲና መብት ጥበቃ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሲሳይ ጥላሁን እንደሚናገሩት፤ የአካል ጉዳት ዕድሜ በገፋ ጊዜ ተደራራቢ ችግር ይሆናል። በመሆኑም የአካል ጉዳት ያለባቸው አረጋውያንን ለመደገፍ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው። አቅም ያላቸው እንደ «አንዲ ማማ» ባሉም ሆነ በሌሎች የግል ድርጅቶች ባሉበት ሆነው እንዲሰሩ ይደገፋሉ። ተግባሩ የሚከወነው ደግሞ ከእነዚህ ዓይነት ተቋማት ጋር በቅንጅት በመሥራት ነው።

እንደ ተቋም የአካል ጉዳት ከሌለባቸው አረጋውያን በተለየ ሁኔታ አካል ጉዳት ያለባቸው አረጋውያን ቅድሚያ አግኝተው የሚደገፉበት ሁኔታ በተቋማቸው አማካኝነት ተመቻችቷል። ለምሳሌ በእርጅና ምክንያት ቤት ከፈረሰባቸው እናቶች የቤቱ መፍረስ አካል ጉዳተኛ አረጋውያን እናቶችን የበለጠ ስለሚያስቸግር በቅድሚያ የእነርሱ ቤት እንዲሰራና እንዲታደስ ይደረጋል። ከላይ ከሚኒስቴር መሥርያ ቤት ጀምሮ በየደረጃው ባለው አረጋውያን የ«ደኃ ደኃ» በሚል ተመልምለው መሥራት ባይችሉም እንኳን የዕለት ጉርሳቸውን እንዲሸፍኑ ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ ተመቻችቷል። ለአካል ጉዳተኛ አረጋውያን ቅድሚያ እንዲሰጥም በአሰራር ተደግፏል።

"በአረጋውያን አያያዝና እንክብካቤ የበለፀጉት ሀገሮች አይታሙም። ከጎለበተ ኢኮኖሚያቸው አንፃር የተሻለ ልምድ አላቸው" የሚሉት አቶ ሲሳይ፤ በእነዚህ ሀገሮች አረጋውያን በልዩ ሁኔታ እንደሚታዩ ያነሳሉ። የሚሰጧቸው ስያሜ በራሱ «የዕድሜ ባለፀጎች» የሚል ክብርና ሞገስ የተሞላበት ነው። ለቀሪ ዘመናቸው ጉልበት የሚቸር ተስፋ ሰጪ ስምም እንደሆነ ይናገራሉ። የበለፀጉት ሀገሮች ምግብና መጠጡን እንዲሁም የመጠለያውን ጉዳይ ተሻግረው የእነሱ አረጋውያኖች የዲጂታላይዜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው የሚያምኑ ናቸው።

እንደ አቶ ሲሳይ ማብራሪያ፤ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ካለንበት ኢኮኖሚያውና ማህበራው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የእኛ ሀገር አረጋውያን የዲጂታላይዜሽን ቴክኖሎጂ መጠቀም ጉዳይ አይደለም። እንኳን አረጋውያኑ ወጣቱም ያለበት በዚህ ልክ ነው ማለት አያስችልም። የእኛ ሀገር የአረጋውያን አንገብጋቢ ጉዳይ የማህበራው ጥበቃ አገልግሎት ስርዓት ተጠቃሚ የማድረግ ጉዳይ ነው። ለዚህ ደግሞ ሴቶችና ማህበራው ጉዳይ ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን ሁሉም በቅንጅት መሥራት አለበት።



**አቶ ሲሳይ ጥላሁን፤**

የአረጋውያንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ብሄራው ማህበራው ጥበቃ ፖሊሲ ላይ የተቀመጡ አምስት የትኩረት መስኮች አሉ። መስኮቹ አካል ጉዳተኞቹን ወይም ሴት አረጋውያንን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም አረጋውያንን የሚመለከቱ ናቸው። እነሱም የመሥራት አቅም ላላቸው አረጋውያን የሴፍትኔት መርሐ ግብር፣ የሥራ ስምሪትና የተሻሻለ የኑሮ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። የጤንነት ሁኔታቸው ካሉበት የዕድሜ ደረጃ አንፃር የተለየ እንክብካቤ የሚፈልግ ነውና የሚያስፈልጋቸውን ማህበራው መድህን መስጠት ግድ ነው። ትራንስፖርት፣ መጠለያ፣ ቤትና ሌሎች መሰረታው አገልግሎቶችን ማግኘት የሚያስችላቸው እንዲሁም በብዙ ተጋላጭ የሆኑበትን ጥቃትና በደልን መከላከል ተገቢ እንደሆነ ያስቀምጣል። ስለዚህም ይህንን ተግባራው ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ያስረዳሉ። እኛም ማህበራው ጥበቃ ፖሊሲው ተግባራው ይደረግና አካል ጉዳተኛ አረጋውያን መፍትሄ ይሰጣቸው በማለት ለዛሬ አበቃን። ሰላም!!

# ዓለም አቀፍ

## የምዕራባውያን ልዩ ተዋጊዎች በዩክሬን መኖራቸውን ሾልኮ የወጣ ሰነድ አጋለጠ

ሾልኮ የወጣ ሚስጥራዊ ሰነድ የአሜሪካ እና የዩናይትድ ኪንግደምን ጨምሮ ምዕራባውያን ልዩ ኃይሎች በዩክሬን ኦፐሬሽን ላይ እንደሚገኙ አጋለጠ። መጋቢት 14 ቀን 2015 ዓ.ም. የሚል ቀን የሰፈረባቸው ሰነዶች በዩክሬን የሚገኙ ትልቁን ቦታ የሚይዙት የዩናይትድ ኪንግደም ወታደሮች መሆናቸውን አሳይቷል።

ዩኬ 50፣ የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) አባል የሆነችው ላትቪያ 17፣ የፈረንሳይ 15፣ የአሜሪካ 14 እና ኔዘርላንድስ 1 ተጠባባቂ ልዩ ኃይል አባላት በዩክሬን መኖራቸውን አሳይቷል። ሰነዶቹ ለአንድ ዓመት ያክል የነበረውን ጥርጣሬ ያረጋገጡ ሆነዋል። ሾልከው የወጡት ሰነዶች "ጥብቅ ምስጢር" ተብለው የተጻፈባቸው ሲሆን፤ በዩክሬን ስላለው ጦርነት በዝርዝር ከማሳየታቸው በተጨማሪ፤ ኪዬቭ የሩሲያ ጥቃት ለመመከት እያደረገችው ስላለው የመልሶ ማጥቃት ዕቅድ ይዘረዝራል።

የአሜሪካ መንግሥት ሰነዶቹ እንዴት አደባባይ ሊወጡ እንደቻሉ ምርመራ እያደረኩ ነው ብሏል።የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስትር ላሎይድ አስቲን የአገሪቱ ፍትሕ ቢሮ የወንጀል ምርመራ ማድረግ መጀመሩን እና ሰነዶቹን ይፋ ያደረገውን ለመለየት ቁርጠኛ መሆኑን ተናግረዋል።

"ምርመራ ማድረጋችንን እንቀጥላለን። ምንጩን እና ስፋቱን እስክንደርስበት ድረስ የማንፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም" ብለዋል። ሰነዶቹ ምዕራባውያኑ ልዩ ኃይል አባላት በየትኛው የዩክሬን ክፍል እንደሚገኙም ሆነ በጦርነቱ ያላቸው ተሳትፎ ምን እንደሆነ ያሉት ነገር የለም። በዩክሬን አሉ የተባሉት ምዕራባውያኑ ልዩ ኃይል አባላት በቁጥር አነስተኛ ይሁኑ እንጂ ውጤታማ እንደሆኑ ይታመናል።

ሩሲያ ከዚህ ቀደም እየተዋጋው ያለሁት ከዩክሬን ጋር ብቻ ሳይሆን ከኔቶ ጋር ጭምር ነው ብላ ነበር።የዩናይትድ ኪንግደም መከላከያ ሚኒስቴር በጉዳዩ ላይ ያለው ነገር የለም። ይሁን እንጂ ትናንት ማክሰኞ በትዊተር ገጹ ሚስጥራዊ ሰነዶች ተብለው የሚጋሩ ሰነዶች "ከፍተኛ ስህተት" ስለሚኖራቸው አንባቢዎች ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል ብሏል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስለየትኛው ሚስጥራዊ ሰነድ እንደሆነ በግልጽ ያለው ነገር የለም። የዩኬ መከላከያ ሚኒስቴር ይህን ይበል እንጂ የፔንታጎን ኃላፊዎች ሰነዱ ትክክለኛ ስለመሆኑ መናገራቸው እየተዘገበ ነው። የዩኬ ልዩ ኃይል አባላት በተለያዩ ዘርፎች ከፍተኛ እውቀት እና ክህሎት ባላቸው የጦር አባላት የተዋቀረ ሲሆን፤ ስብስቡ በዓለም ላይ ትልቅ አቅም አላቸው ከሚባሉት መካከል አንዱ ነው። አሜሪካ እና ዩናይትድ ኪንግደም በሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ጠንካራ የዩክሬን አጋር ከሆኑ አገራት መካከል መሆናቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።





## ጀርመን የቻድ አምባሳደር በ48 ሰዓት ከአገር እንዲወጡ አዘዘች

አፍሪካዊቷ አገር ቻድ ባለፈው ሳምንት የጀርመን አምባሳደርን ማባረሯን ተከትሎ ጀርመንም በአጸፋው የቻድ አምባሳደር በ48 ሰዓታት ከአገር እንዲወጡ አዘዘች። የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትናንት ማክሰኞ ባወጣው መግለጫ የቻድ አምባሳደር ማሪየም አሊ ሙሳ በ48 ሰዓት ውስጥ ከጀርመን ለቀው መውጣት አለባቸው ብሏል።

"ጉዳዩ እዚህ ደረጃ በመድረሱ አሳዝኖናል" ሲል የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በትዊተር ገጹ አስፍሯል። በቻድ የጀርመን አምባሳደር ጃን ክርስቲያን ጎርደን ወታደራዊው መንግሥት ከቻድ ካባረራቸው በኋላ ባለፈው ዕሁድ አገሪቱን ለቀው ወጥተዋል።

ቻድ "አምባሳደሩ ቀናነት የጎደለው አመለካከት አላቸው" እንዲሁም "ለዲፕሎማሲያዊ ልምድ ክብር የላቸውም" በሚል ከአገር መባረራቸውን አስታውቃ ነበር። አጠር ያለው የቻድ መንግሥት መግለጫ ይህንን ከማለት በስተቀር አምባሳደሩ የተባረሩበትን ምክንያት በዝርዝር አላስቀመጠም።

የጀርመን ባለስልጣናትም ቻድ አምባሳደሩን ያባረረችበትን ምክንያት እንዳልገለጸች አስታውቃለች።"አምባሳደሩ በንጃሚና [የቻድ ዋና ከተማ] አርአያ በሚሆን መንገድ ስራቸው እየሰሩ ነበር። በቻድ ለሰብዓዊ መብት መከበርና ለፈጣን የሲቪል መንግሥት ሽግግር ሰርተዋል" ሲል የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገልጿል።

እንደ አውሮፓውያኑ በ2021 በቻድ ስልጣን ላይ የነበሩት ኢድሪስ ዴቢይ ኢንቶ መገደላቸውን ተከትሎ ልጃቸው ጀነራል ማሃማት ኢድሪስ ዴቢይ ስልጣን ላይ ወጥተዋል። በአባታቸው የተተኩት ጀነራል በአገሪቱ ምርጫ እስኪካሄድ ጊዜያዊ መሪ ሆነው ለ18 ወራት አገር ያስተዳድራሉ ተብሎ የነበረ ቢሆንም ቻድ አሁንም በወታደራዊ አስተዳደር ስር ትገኛለች።

በአገሪቱ ሊካሄድ የነበረው ምርጫ እንዲዘገይ መደረጉ ሕዝባዊ ተቃውሞን አስከትሏል። የቻድ ወታደራዊ መንግሥት በሚቀጥለው ዓመት ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የማድረግ ዕቅድ አለኝ ማለቱን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት



## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዓለም ቻምፒዮና ታሪክ በምርጦች ዝርዝር ታጭተዋል

ብርሃን ፈይሳ

የዓለም አትሌቲክስ ከጥቂት ወራት በኋላ በሃንጋሪ ቡዳፔስት በሚያካሂደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና 40ኛ ዓመቱን ያከብራል። ይህንን ክብረ በዓል ተከትሎም የዓለም አትሌቲክስ የተለያዩ መርሃ ግብሮችን ከወዲሁ ማዘጋጀት ጀምሯል። ከእነዚህም መካከል አንዱ ባለፉት 18 ቻምፒዮናዎች የታዩ ምርጥ ክስተቶችንና የአስደናቂ ታሪኮች ባለቤት የሆኑ አትሌቶችን ማስመረጥ ነው።

ከሰሞኑ ይፋ የተደረገው ይህ ምርጫ በኢንተርኔት ተደግፎ በደጋፊዎች ድምፅ የሚሰጥበት ሲሆን፤ 40 የሚሆኑ አትሌቶችና አስደናቂ ገድሎቻቸው በሁለቱም ጾታ ተዘርዝረዋል። ከእነዚህ መካከልም አንድ መራጭ በሁለቱም ጾታ ለአስር አስር አትሌቶች ድምጽ የሚሰጥ ይሆናል። አሸናፊዎቹም በሃንጋሪዋ ቡዳፔስት በሚከናወነው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ ይፋ ይሆናሉ። ከመራጮች መካከል ሁለት የሚሆኑት ደግሞ በዓለም አትሌቲክስ ሙሉ ወጪያቸው ተሸፍኖ በቻምፒዮናው የመታደም ዕድል ያገኛሉ።

የዓለም አትሌቲክስ እስካሁን በተካሄዱ የዓለም ቻምፒዮናዎች አስደናቂ ክስተቶች ናቸው ብሎ በዝርዝር ካቀረባቸው መካከልም ኢትዮጵያውያን ድንቅ አትሌቶች ተካተዋል። በዝርዝሩ ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ምክትል ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፣ ገዛኸኝ አበራ፣ ጥሩነሽ ዲባባ እና ቀነኒሳ በቀለ ተካተዋል። ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ በተለየ መልኩ እ.አ.አ በ2003ቱ የፓሪስ እና በ2009 የበርሊን ቻምፒዮናዎች ላይ ባሳየው አቋም ሁለቴ ሊመረጥ ችሏል። ኢትዮጵያ በዚህ ቻምፒዮና ተሳትፎዋን ከመነሻው (እ.አ.አ በ1983 ፊንላንድ) ስታደርግ፤ ማራቶንን ሁለተኛ ሆኖ በገባው አትሌት ከበደ ባልቻ የመጀመሪያውን ሜዳሊያም አሳክታለች። ባለፉት 18 ቻምፒዮናዎችም 33 የወርቅ፣ 34 የብር እና 28 የነሐስ በጥቅሉ 95 ሜዳሊያዎች ተመዝግበዋል።



የምንጊዜም የረጅም ርቀት ከዋክብት አትሌቶች ኃይሌ ገብረሥላሴና ደራርቱ ቱሉ በዓለም ቻምፒዮና ከምርጦች ዝርዝር ተካተዋል፣

አትሌቶቹ ሜዳሊያዎችን ከማስመዝገብ ባለፈ ያሳዩት ብቃት ደማቅና የማይረሳ ታሪክ ሆኖ ሊመረጡ ችለዋል። እ.አ.አ በ1999 በስፔኗ ሴቪሌ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ ሁለት የወርቅ ሜዳሊያዎችን ስታስመዘግብ አንደኛው የተገኘው በምንጊዜም ምርጡ አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ ነበር። እ.አ.አ ከ1993 የስቱትጋርት ቻምፒዮና አንስቶ በዚህ ውድድር ተካፋይ የነበረው ኃይሌ በተከታታይ በ10ሺ ሜትር ሊደፈር የማይችል አትሌት መሆኑን አስመስክሯል። አራተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀበትን ውድድርም ዓለም አቀፉ ተቋም ታሪካዊ ከሆኑ ክስተቶች መካከል አካቷል።

ቀጣዩ ቻምፒዮና እ.አ.አ በ2001 ካናዳ ኤድመንተን ላይ ነበር የተካሄደው። በዚህ ቻምፒዮናም አሁን ላይ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን በመምራት ላይ የሚገኙት ምክትል ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ እና ምክትል ፕሬዚዳንቱ ገዛኸኝ አበራ ነበሩ የወርቅ ሜዳሊያዎች ያሳኩት። በሴቶች 10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤቷ ደራርቱ ቱሉ በቻምፒዮናው አሸናፊ የሆነችው ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ ሲሆን፤ ከወሊድ መልስ በአስደናቂ አቋም በኦሊምፒክና የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና ላይም አስደማሚ ብቃት ነበር ያሳየችው። አትሌት ብርሃኔ አደሬ እና ጌጤ ዋሚም ተከትለዋት በመግባት ሜዳሊያዎቹን ጠራርገው የወሰዱበት አስደሳች ውድድር በመሆኑም በበርካቶች ዘንድ ይታወሳል።

ከረጅም ዓመታት በኋላ ኢትዮጵያ ዳግም በኦሊምፒክ ማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ ያሳካችው ሲድኒ ላይ ነበር። የሜዳሊያው ባለቤት ገዛኸኝ አበራ የሰራው ገድል ሳይቀዘቅዝ በዓመቱ ኤድመንተን ላይ ዳግም ቻምፒዮን በመሆንም በርካቶችን አስደንቋል። እጅግ ፈታኝ በነበረው ውድድር ገዛኸኝ ኬንያዊውን አትሌት በአንድ ሰከንድ ቀድሞ በመግባትም ነበር አሸናፊነቱን የተቀዳጀው። ከፍተኛ ጽናትና አቅም በሚጠይቀው ማራቶን በተከታታይ ዓመት በሁለት ትልልቅ ውድድሮች አሸናፊ መሆን ደግሞ የተለየ ብቃት የሚጠይቅና የምንጊዜም ጀግና የሚያሰኝ በመሆኑ ለምርጫ ቀርቧል።

ፊር ቀዳጇ ሄልሲንኪ ቻምፒዮናውን ለሁለተኛ ጊዜ ባዘጋጀችበት 2005 በሴቶች 5ሺ እና 10ሺ ሜትር ተዓምር ነበር የታየው። በሁለቱም ርቀት ኢትዮጵያውያኑ ከወርቅ እስከ መዳብ ያሉ ሜዳሊያዎችን ጠራርገው ሲወስዱ፤ የጥንካሬ ተምሳሌቷ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ደግሞ በሁለቱም ርቀት ወርቅ ያጠለቀች የመጀመሪያዋ አትሌት በመሆን አስደናቂውን ገድሏን አጽፋለች። አይረሴ በሆነው በዚህ የአትሌቷና የዓለም ቻምፒዮና ታሪክ ታላቅ እህቷ እጅጋየሁ ዲባባ ደግሞ ተከትላት በመግባት ሁለት የነሐስ ሜዳሊያ ማጥለቋ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ የሚታወስ ነው።

ጀግናው የረጅም ርቀትና የማራቶን አትሌት ቀነኒሳ በቀለ በኦሊምፒክ፣ በዓለም ቻምፒዮና እና በአገር አቋራጭ ቻምፒዮናዎች የሠራቸው ጀብዱዎች ተዘርዝረው አያልቁም። በዚህ የውድድር መድረክ 6 ሜዳሊያዎችን ያስቆጠረው አትሌቱ፤ መነሻው እ.አ.አ የ2003ቱ የፓሪስ ቻምፒዮና ነበር። የታላቁ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ ተተኪ መሆኑን ባስመሰከረበት በዚህ ውድድር የ10ሺ ሜትር አሸናፊ ሲሆን በ5ሺ ሜትር ደግሞ የነሐስ ሜዳሊያ ነበር ያገኘው። ከሄልሲንኪ እና ኦሳካ በመቀጠልም በ2009 በርሊን ላይ ዳግም በሁለቱም ርቀት አሸናፊ በመሆን ሌላ ክብር ደርቧል። ቀኒሳ ከድሉ ባሻገር በ10ሺ ሜትር የውድድሩን ክብረወሰን በማሻሻልም ቻምፒዮናው ከማይረሱት መካከል አንዱ እንዲሆን አድርጓል።


## INVITATION FOR INTERNATIONAL COMPETATIVE BIDDING (ICB)

JERR P.L.C established under Commercial Laws of Ethiopia and engaged in Agriculture, Import & Export, Construction, Manufacturing business is interested to purchase a 10 **TPH** CORN-SOYABEAN BLEANDING ++ ( CSB++), 20TPH MASH and 10TPH Pellet Animal Feed Processing Plant.

We hereby invites interested Bidders to submit their **Technical** and **Financial** offer separately for CSB++ and Animal Feed processing Plants with accessories on turnkey Project basis.

| Lot No | Tender No | Description | Bid Security Amount (ETB or Equivalent) |
|---|---|---|---|
| Lot I | JFPDB 01/2023 | 10 TPH CSB ++ Processing Plant | 200,000.00 |
| Lot II | JFPDB 02/2023 | 10 TPH Pellet and 20TPH Mash animal feed Processing Plant | 200,000.00 |

Interested Bidders are invited to apply to participate in this ICB considering the following points:-

1. Qualified bidders can obtain the ICB documents from Jerr PIC, HQ located in front of African Union HQ, Amaga Building, 6th Floor, during working Hours (8:00 AM-5:00 PM) from Monday to Saturday (8:00 AM-12:00 AM).
2. The Bid Security shall be CPO or unconditional Bank Guarantee in the name of Jerr Plc.
3. Bids shall be submitted jn wax sealed, three envelope systems, #1. Technical offer, #2. Financial offer and #3. Bid security in one original and one copy each at the address indicated under 7 & 8 below.
4. The financial bid shall be submitted in US$ or any other convertible currency separately
5. Bidders shall attach their trading license and related relevant documents with the technical offer separately.
6. The least bidder will be determined as per the Evaluation Criteria set with the combined sum of the Technical and Financial scores.
7. Bidders shall submit their bids during office hours from Monday to Friday to Development Bank of Ethiopia's (DBE), Head Office, Near Kazanchis, Yosep Tito street, ground floor, Addis Ababa, Ethiopia, before 10:00 AM, May 31st 2023.
8. The bid will be closed on May 31st, 2023 at 10:00 AM and opened at 10:30 AM in the presence of bidders or their representative who is interested to attend, at Development Bank of Ethiopia's (DBE), Head Office, Near Kazanchis, Yosep Tito street, ground floor, Addis Ababa, Ethiopia
9. Jerr Plc has the right cancel, to accept or reject the entire or partial part of this bid.

If you require further clarification or information, please contact our office or call through +2519304804 / +251909549154 or email : bewm2006@gmail.com /allenemolla1957@gmail.com

**JERR P.L.C**